ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል


በ


ሚካኤል ክፍሌ


ግንቦት /2015ዓ.ም

ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

# በምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሀን ወረዳ የሰርግ ስነስርአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን አንጻር

በ

ሚካኤል ክፍሌ

የጥናቱ አማካሪ

መምህርት ሄለን ገ/ስላሴ

ለአርትስ ኦፍ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ

ግንቦት/2015ዓ.ም

# የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በወልቂጤ ዩንቨርሲቲ  የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለው፡፡

የአማካሪው ስም........................

ፊርማ..................................

ቀን..................................

ይህ ጥናት "በምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሀን ወረዳ የሰርግ ስነስርአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን አንጻር " የመጀመሪያ  ድግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሁፍ ዩኒቨርሲቲውን ጥራት ደረጀ ያሟላ እና ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህም በፈታኝ ኮሚቴው ተረጋግጧል፡፡

ፈታኝ አንድ

ስም......................................

ፊርማ.....................................

ቀን.......................................

ፈታኝ ሁላት

ስም......................................

ፊርማ...............................

ቀን..................................

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ለድንግል ማርያም ልጅ ለልዑል እግዚአብሔር ክብርእና ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ እንዳዘጋጅ መረጃ በመስጠት እና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላገዙኝ ለአባቴ ለመምህር ክፍሌ ሽፈራዉ እና ለመምህር አለሙ ሰዉነት አመሰግናለሁ፡፡ በመጨረሻም በማማከር ላገዙችኝ ለመምህር ሄለን ገ/ስላሴ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አበርክቶ

በብዙ ፈተና ውስጥ እኔን ደስተኛ ለማድረግ የራሷን ደስታ ለዘነጋችው ለእናቴ ብርቱካን ይበልጣል  እና ለአባቴ ለመምህር ክፍሌ ሽፈራዉ አበረክታለሁ።

## አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት የሚያተኩረው በምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሀን ወረዳ የሰርግ ስነስርአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን አንጻር ላይ ሲሆን የፈለገ ብርሀን ወረዳ የጋብቻ ስነ-ስረአት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ የሚዳስስ እና የሚተነትን ጥናታዊ ፅሁፍ ነው። አጥኚው ጥናቱን ለማጥናት የተጠቀመው የጥናት አይነት ገላጭ የምርምር ዘዴ ሲሆን መረጃ ለመሰብሰብ የተጠቀመባቸው ዘዴዎችም ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ናቸው ። ስለ ፈለገ ብርሀን ወረዳ ጋብቻ ስነ-ስረአት እውቀት ያላቸውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና የአጥኚውን ምልከታ ተጠቅሟል ። እንዲሁም ስለ ትውፊታዊ ተውኔት የተፃፉ መፅሀፍትን እና ጥናታዊ ፅሁፎችን በመዳሰስ ጥናቱ ተጠንቷል ። ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ አራት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በምዕራፍ አንድ የጥናቱን ዓላማ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ዘዴ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች እና የጥናቱን አደረጃጀት የሚያሳይ ነው። አጥኚውም እነዚህን የማስረጃ ምንጮችን በዋናነት በምዕራፍ ሁለት በስፋት ያካተተ ሲሆን በርዕሱ ላይ ያተኮረውን እና የጥናታዊ ጽሁፉ ዋና የመረጃ የትንተና ክፍል በምዕራፍ ሶስት በዝርዝር ይተነትናል። በምዕራፍ አራት አጥኚው የማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ ናቸው ያላቸው ነጥቦች ያስቀምጧል። አጥኚው እንደመረጃ ምንጭ የተጠቀማቸውን የመረጃ ምንጮ በጥናታዊው ጽሁፍ መጨረሻ አስፍሯል።

# ሙዳየ ቃላት

ጀንዲ.......................................................................... .ከሰንጋ በሬ ታርዶ የሚገፈፍ ቆዳ ነው፡፡

ዋንጫ...........................................................................ከከብቶች ቀንድ የሚሰራ ለመጠጫ የሚያገለግል እቃ ነው፡፡

**ጫጉላ ........................................................................ ከባህር ዛፍ ቅጠልና ከገለባ የሚሰራ ትንሽ ቤት፡፡ ሙሽሮች የመጀመሪያ ግንኙነታቸዉን የሚያደርጉበት ቦታ ነዉ**

ማውጫ

ምስጋና ............ II

አበርክቶ ............ III

አጠቃሎ ............ IV

ሙዳየቃላት ............ V

ምዕራፍ አንድ ............ - 1 -

1 መግቢያ ............ - 1 -

1.1 የጥናቱ ዳራ ............ - 1 -

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ - 2 -

1.3 የጥናቱ አላማ ............ - 3 -

1.3.1 የጥናቱ አብይ አላማ ............ - 3 -

1.3.2 የጥናቱ ንዑስ ዓላማ ............ - 3 -

 የወረዳዉን የሰርግ ስነስረዓት ማሳየት ............ - 3 -

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ ............ - 3 -

1.5 የጥናቱ መጠነ ራዕይ ............ - 4 -

1.6 ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቂዎች ............ - 4 -

1.7 የጥናቱ ዘዴ ............ - 4 -

1.7.1 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ............ - 4 -

1.7.1.1 ምልከታ ............ - 4 -

1.7.1.2 ቃለ-መጠየቅ ............ - 5 -

1.8 የጥናቱ አወቃቀር ............ - 5 -

1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው ............ - 6 -

ምዕራፍ ሁለት ............ - 7 -

2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ............ - 7 -

2.1.1 የተውኔት ምንነት ............ - 7 -

2.1.2 የትውፊታዊ ተውኔት ምንነት ............ - 8 -

2.1.3 የትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን - 8 -
2.1.3.1 መቼት - 9 -
2.1.3.2 ቃለ-ተውኔት - 10 -
2.1.3.3 ቁሳቁስ - 12 -
2.1.3.4. አልባሳት - 12 -
2.1.3.5 ታሪክ - 13 -
2.1.3.6 ሚና ክፍፍል - 14 -
2.1.4 ሰርግ ምንነት - 16 -
2.2 የተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፎች ቅኝት - 16 -
ምዕራፍ ሶስት - 18 -
3. የመረጃ ትንተና - 18 -
3.1 የፈለገ ብርሃን ወረዳ መልካ ምድራዊ ዳራ - 18 -
3.2 የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነረዓት ክንዉን - 19 -
3.3 "የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት ከትዉፊታዊ ተዉኔት አላባዉያን አንፃር" - 22 -
3.3.1 መቼት - 22 -
3.3.2 ቃለ- ተዉኔት - 23 -
3.3.3 ቁሳቁስ - 25 -
3.3.4 ግብአተ ድምፅ - 27 -
3.3.5 አልባሳት - 28 -
3.3.6 ሚና ክፍፍል - 29 -
ምዕራፍ አራት - 30 -
ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሃሳቦች - 30 -
4.1 ማጠቃለያ - 30 -
4.2 የመፍትሔ ሀሳቦች - 31 -
ዋቢ መፃህፍት - 32 -

# ምዕራፍ አንድ

## 1 መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ተውኔት የሰውን ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ወደ መድረክ በማምጣት የሚሰራ ሲሆን በውስጡም የተለያዩ ተውኔታዊ ዘውጎች አሉት፡፡ ፋንታሁን እንግዳ በ "የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ›› በሚለው መፅሀፍ ላይ እንዲህ እንደገለጸዉ ፡፡

> *"ተውኔታዊ ዘውግ ማለት ፃሀፊ ተውኔቱ አንድን ርዕሰ ጉዳይ መሰረት፡፡ በማረግ ፅፎ የሚያቀርብበት የተውኔት ዘር መሆኑን እና በውስጡም ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚከፈል ያትታል፡፡ በቅርፅ ዙርያ ነው፡፡ የመድረክ ተውኔት፣ የሬድዮ ተውኔት፣ ሙዚቃዊ ስንመለከት ታሪካዊ ተውኔት፣ ሀይማኖታዊ ተውኔት፣ አብዮታዊ ተውኔት እንዲሁም ትውፊታዊ ተውኔት በዚሁ በጭብጣዊ ዘውግ ስር ይፈረጃሉ በማለት ይገልፃል"*(2005፤81)

ትውፊት ማለት የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ የአኗኗር ዘይቤን የሚያንፀባርቅ ክዋኔ ነው፡፡ ፈንታሁን እንግዳ ‹‹ ተውኔት መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው ›› በሚለው መፅሀፋቸው ላይ እንዳስቀመጡት፡-*‹‹ትውፊት ማለት ካለፈው ወይም ካለፈው ትውልድ የተወረሰና ዘመነኛ ደራሲዎች በጥናት ምርምር የሚመሩበት እምነት፣ ስነ-ቃል፣ አስተሳሰብና የመሳሰሉትን ያካታል፡፡(1993፤92)*

*በተጨማሪም ዊኪፒድያ የተሰኘው ድህረ ገፅ ትውፊትን ሲገልፀው፡- "ትውፊት ማለት የአንድ ቤተሰብ ወይም ቡድን አልያም ማህበረሰብን እምነት/ወግ ከትውልድ ወደ ትውለድ የሚያስተላለፍ ክዋኔ ነው"፡፡*

ትውፊት በዚህ ትርጓሜ ስንመለከትው ትውፊታዊ ተውኔት ስንል ደግሞ የአንድን ማህበረሰብ አኗኗር ዘይቤ እና ልማድ ላይ መሰረት ያደረገ ክዋኔ ወይም ትርኢት ነው፡፡

ይህንንም ፈንታሁን እንግዳ ‹‹ ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው›› በሚለው መፅሀፋቸው ውስጥ ይህንን ገለፃ አስቀምጠዋል፡፡

> “የትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን በደራሲው ምናብ የሚፈጠሩ ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወረሱ የተሸጋገሩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ትውፊት የሚለው ቃል የሚፈጠርን ሳይሆን የሚሰሩትን አለባዎችን ያመለክታል”፡፡(1993፤94)

በማለት ይገልጸዋል፡፡ ትወፊታዊ ተውኔት መሰረት ከሚያደርገው የአንድን ማህበረሰብ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ማለትም ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ የአኗኗር ዘይቤን እንዲሁም የተለያዩ የማህበረሰቡ ክዋኔዎች፣ የአምልኮ ስረዓት፣ የግጭት አፈታት፣ የሰርግ ስነ ስረዓት እንዲሁም የተለያዩ ባህላዊ ክዋኔዎችን መሰረት አድርጎ ይከውናል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትታወቅባቸው የራሷ የሆኑ ባህሎች፣ ቅርሶች፣ እሴቶች ያሏት ሀገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ ብዙ ብሄር ብሄረሰቦች የሚኖሩባት ህብረብሄራዊ ሀገር ነች፡፡ እነዚህም ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸው የሆነ ባህል ቢኖራቸውም አንድ ማህበረሰብ ከሌላው ማህበረሰብ የሚለዩበት የራሳቸው የሆነ መገለጫዎች ወይም እሴቶች አላቸው፡፡ ከነዚህም ህዝቦች መካከል የአማራ ብሄር ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሃን ወረዳ ህዝቦች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህም ማህበረሰቦችም እንደሌሎች ማህበረሰቦች ራሳቸው የሆነ ባህል ታሪክ ወግ እንዲሁም ተፈጥሯዊ እሴቶች የያዘ የአኗኗር ስርአት ይከተላሉ፡፡ በማህበራዊ ህይወታቸው የሚያከናዊኗቸው ትውፊታዊ እሴቶች መካከል ሀይማኖታዊ ስርአቶች የለቅሶ ስርአቶች የሰርግ ስርአቶች እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡ የሰርግ ስነስርአታቸውን ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተወራረሰ አሁን እሳከለንበት ዘመን ድረስ ማህበረሰቡ እየተገለገለት ይገኛል፡፡የዚህ ጥናት አጥኚም በአማራ ክልል ከሚገኙት ማህበረሰቦች መካከል አንዱ የሆነውን የፈለገ ብርሃን ወረዳ ማህበረሰብ የሰርግ ስነ ስርዓት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር ይፈትሻል ፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህንን ጥናት ለማጥናት ያነሳሱኝ ምክንያቶች ወረዳው ብሎም ማህበረሰቡን እንዲሁም ባህሉን ከማስተዋወቅ አንፃር ትልቅ አስተዋጦ ይኖረዋ ብሉ በማሰብ እና የወረዳውን የሰርግ ስነስረዓት ለማሳወቅ እና ባህሎ እንዳይረሳ ለማድረግ ነዉ፡፡ በተጨማሪ አጥኚው ይህን ጥናታዊ

ጽሁፍ ለመስራት ያነሳሳው ምክንያት የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነስርአት ከማሳወቅ ባሻገር ባህሉ ያለው ተጨባጭ ነገር ለሌሎች ለማሳወቅ ነው፡፡

## *1.3 የጥናቱ አላማ*

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በውስጡ አብይና ንዑስ አላማዎችን አካቶ የያዘ ነው፡፡

### 1.3.1 የጥናቱ አብይ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አላማ በምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሃን ወረዳ ውስጥ ስለሚካሄደዉ የሰርግ ስነ ስርአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን አንጻር መተንተን ነው፡፡

### 1.3.2 የጥናቱ ንዑስ ዓላማ

- ✓ የወረዳዉን የሰርግ ስነስረዓት ማሳየት
- ✓ በሰርግ ስነስረዓቱ ላይ የሚነገሩ ስነ ቃሎችን ለይቶ ለመግልጥ
- ✓ በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነ ስርአት መግለጽ

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት  በምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነስረዓት ላይ መጠናቱ በርካታ ጠቀሜታወች ይኖሩታል ፡፡

- ✓ በምስራቅ ጎጃም ዞን በፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነስርአት ላይ ለማወቅ ለሚፈልጉ ሌሎች አጥኚዎች እንደመረጃ ለማቅረብ፡፡
- ✓ በፈለገ ብርሃን ወረዳ የሚካሄደውን የሰርግ ስነ ስርአት ለሌላው ማህበረሰብ ለማሳወቅና እንደመረጃ ለማቅረብ ፡፡
- ✓ ባህሉ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀዘቀዘ ለመምጣቱ ባህሉ እንዳይረሳ ለማድረግ ፡፡

## 1.5 የጥናቱ መጠነ ራዕይ

ይህ ጥናት ትውፊታዊ ጥናት ሲሆን ትኩረት አድርጎ የሚያጠናውም ይህም ጥናት ምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስርዓት ከትውፊታዊ ተዉኔት አላባዉያን አንፃር ብቻ ትኩረት አድርጉ ለይቶ ይተነትናል።

## 1.6 ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቂዎች

- ✓ በምስራቅ ጎጃም ዞን በፈለገ ብርሃን ወረዳ ወጣቶች በአካባቢዉ የሚካሄደዉን የሰርግ ስነስረዓት እንዴት ይከበራል?
- ✓ በምስራቅ ጎጃም ዞን በፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነስረዓት ከሌሎች ባህሎች የሚለይበት ነገር አለ ወይ።ለምን?

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

አጥኚው ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ለመስራት ገላጭ የምርምር ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን ገለጻዊ የምርምር አይነት ዋና አላማዉን መገለጽና ግኝቶችን በማረጋገጥ ማስረዳት ነው። አለም እሸቱ "መሰረታዊ ምርምር ዘገባ አጻጻፉ" በሚለው ገለጻዊ ምርምርን እነዲህ ገልጸዋል። "ገለጻዊ የምርምር ገለጻን፣ ትንታኔንና አተረጓጎምን መሰረት ያደረገ ነው" በሚል ያስቀምጠዋል። (1994-148) ዓ.ም

አጥኚው ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ገላጭ በማድረግ ቃለ መጠየቅ ምልከታንና ትውፊታዊ ተውኔት የተጻፉ መጽሐፍትን በማንበብ እንዲሁም የተዛማጅ ፁሁፍ ቅኝት በማደርግ ጥናቱን አጥንቷል።

### 1.7.1 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

አጥኚው ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ የተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢ ዘዴዎች በዋናነት ምልከታንና ቃለ መጠየቅን ናቸዉ።

#### 1.7.1.1 ምልከታ

ምልከታ በአይናችን የምናየዉ ነገር ሲሆን ይህም ማለት አንድ ደርጊት ሲካሄድ በቦታዉ በመገኘት በአይናችን የምንመለከትበት መንገድ ነው።አለም እሸቱ "መሰራታዊ የምርምር ዘገባ አጻጻፍ " በሚለው መጽሐፍ ስለ ምልከታ እንዲህ ሲል ገልጿል።"ምልከታ አይተን የምናልፈው

ሳይሆነ ለታቀደለት መሰረታዊ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሲባል መከናወን ትኩረትና ምርምርን የሚጋብዘን የመሰብሰቢያ  ስልት ነው፡፡" (1994-69) ዓ.ም

አጥኚው ጥናቱን በሚያደርግበት ወቅት የሰርግ ስነስርአት በሚካሄድበት ቦታ በመሄድ እና የክንውኑ ተሳታፊ በመሆን ተመልክቷል፡፡ ከሚመልከተዉ ነገሮች ዉስጥ በስነስረዓቱ የሚለበሱ አልባሳትን ፣ ድርጊቶችን፣ ቃለ ተዉኔቶችን፣ የሚጠቀሙትን ቁሳቁስ እንዲሁም እያንዳንዱ ሰዉ የሚሰራዉ የስራ ድርሻ እና የመሳሰሉትን በመሄድ ተመልክቷል፡፡

### 1.7.1.2 ቃለ-መጠየቅ

ቃለ መጠየቅ በአካል በመገኘት እንዲሆም ቀጥታ በስልክ በመደዉል ከሰዎች መርጃ የመንሰበስብበት መንገድ ነው፡፡ አለም እሸቱ "መሰረታዊ የምርምር እና ዘገባ አጻጻፍ" በሚለው መጽሀፍ ስለ ቃለመጠይቅ እንዲህ ሲል ገልጿል፡፡ "ቃለ መጠይቅ ጠያቂው ከተጠያቂው ጋር በግንባር ተገናኝቶ በጽሁፍ ሳይሆን በቃለ ምልልስ የሚሰጣጡበት ሂደተ ነው፡፡" (1994-65) ዓ.ም

አጥኚው በወረዳው ያሉ ማህበረሰቦችንና የባህሉ ባለቤቶችን በመጠየቅ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችሏል፡፡ የአካባቢዉ ተወላጅ እና ሰለማህበረሰቡ ጥልቅ እውቀት ያላቸዉን ሰዎች የአማረኛ መምህራን  በተጨማሪ ስለ ማህበርሰቡ ጥልቅ እዉቀት ያላቸዉ እና በዓሉ የሚመልከታቸዉን ሰዎች ጠይቋል፡፡

## 1.8 የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ መግቢያ፡- የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አብይና ንኡስ አላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ መጠነ ራእይ እና የጥናቱ አስፈላጊነት፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄወች፣ የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች እና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሄ ሀሳቦችን ይይዛል፡፡ በምዕራፍ ሁለት፡- የንድፉ ሀሳብ ቅኝት፣ የተውኔት ምንነት፣ የትውፊታው ተውኔት ምንነት፣ የሰርግ ምንነት፣ የትውፊታዊ ተወኔት አላባዉያን፣ መቼት፣ቃለ ተውኔት፣ ቁሳቁስ፣ አልባሳት፣ ታሪክ፣ ሚና አከፋፈል፣ የተዛማጅ ጥናታዊ ፁሁፍ ቅኝት አካቷል፡፡ ምዕራፍ ሶስት፡- የመረጃ ትንተና፣ የፈለገ ብርሃን ወረዳ መለክዓ ምድራዊ ዳራ፣ የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ አይነት፣ የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነስርአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን መተንተን፣ መቼት፣ ቁሳቁስ፣

ግብአተ ድምጽ፣ አልባሳት፣ ዘፈንና ሚናክፍፍል ይገኝበታል፡፡ በምዕራፍ አራት፡- ማጠቃለያ፣ የመፍትሔ ሀሳቦች እና ዋቢ መጻሕፍትን አካቶ ይይዛል፡፡

## 1.9 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄዎቻቸው

አጥኝው ይህን ጥናት ሲያጠና በርካታ ችግሮች ገጥመውታል፡፡ በጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በፈለገ ብርሃን ወረዳ ስለሆነ አጥኚዉ የሚያጠናበት ቦታ በመራቁ ለጥናቱ ተግዳሮት ፈጥሮበታል ፡፡ከአካባቢው ባለሙያወች ባህልና ቱሪዝም ሃላፊወች ጋር በነበረው ቃለ መጠይቅ ወረዳው ላይ ዶክመንት ተደርገው የተቀመጡ መረጃወች ባለመኖራችው እና የሚፈልገዉን መረጃ በአግባቡ ባለመስጠታቸዉ የሚፈልገውን መረጃ ሙሉ ለሙሉ አለማግኘት ችግር ነበር፡፡ አጥኝው እነዚህን ሁሉ ችግሮች የራሱን መፍትሔዎች ተጠቅሟል፡፡ዋናው እንደ መፍትሄ የሆነው ስለ ሰርግ ስነስረዓት አጥኝው ባለበት ቤተክርስትያናት በመሄድ መጽሃፍትን ተመልክቷል፡፡ ቃለመጠየቁን ለመቅረጽ ስለተቸገረ በስልክ በመስማት በወረቀት በማስፈር አስቀምጧል፡፡ አጥኝው ጥናት በሚካሄዱበት ቦታ ያደገ በመሆኑ በዓሉን በማስታወስም አስቀምትጧል፡፡ በሌላ በኩል ከባህልና ቱሪዝም ሃላፊወች ያልገኘዉን መርጃ ከአካባቢዉ ማህበረሰብ በመጠየቅ አስፍሯል፡፡

# *ምዕራፍ ሁለት*

## *2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት*

### *2.1.1 የተውኔት ምንነት*

ተውኔት የምንኖርበትን ዓለም የህይወት ተግባራትን እየቀዳ በቦታና በጊዜ ተገድቦ ለተመልካች የሚቀርብ ታሪክ ነው፡፡ ተውኔት ማድረግን ወይም መተወንን ያመለክታል፡፡ ስለተውኔት ዘሪሁን አስፋው "የስነ ጽሁፍ መሰረታዊያን" በተሰኘው መጽሀፍ የተውኔት ምንነትን እንዲህ ይገጸዋል፡፡

> *"ተውኔት የራሱ ባህሪያት ያሉት አንድ የስነ ጽሁፍ ዘር ሲሆን እንደሌሎች የስነ ጽሁፍ ዘሮች የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገጽታዎች ያንጸባርቃል፡፡ የተመረጠን የማህበረሰብ ገጽታን በማሳየት ረገድ ከሌሎቹ የስነ ጽሁፍ ዘሮች የሚጋራቸው ኪነ ጥበባዊ ባህሪያት ቢኖሩትም ገና ከመነሻው በተዋኒያኑ አማካኝነት በመድረክ ላይ እንዲቀርብ የሚደርስ በመሆኑ ከሌሎች በአያሌው የተለየ ነው፡፡ ተውኔት በደራሲው ወይንም በጸሀፈ ተውኔቱ በተመረጡ ጠባብ የቦታና የጊዜ ክልል ህይወትን በድርጊት በመድረክ ላይ ስለሚያቀርብ ከቀሩት የስነ ጽሁፍ ዘሮች ይበልጥ ለስሜታችን ቀርበት አለው፡፡"*
> *(2009፣ 261)*

ተውኔት ሰው ልጅ ምድር ላይ ከሚኖረው ህይወት ቆይታ እየተቀዳ ለራሱ ለሰው ልጅ በመድረክ ላይ ይቀርባል፡፡ ተውኔት በመሃበረሰቡ ዘንድ መጥፎ የሚባሉ ድርጊቶችን በተውኔት ውስጥ ያሳያል፡፡ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ተግባራትን እያበረታታ ያስተምራል፡፡ ተውኔት የራሱ ባህሪያት ያሉት አንድ የስነ ጽሁፍ ዘርፍ ሲሆን እንደሌሎች የስነ ጽሁፍ ዘርፎች የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገጽታዎች ያንጸባርቃል፡፡ ተመረጠን ማህበረሰብ ገጽታን በማሳየት ረገድ ከሌሎች የስነ ጽሁፍ ዘርፎች የሚያጋራቸው የኪነጥበባዊ ባህርያት ቢኖሩትም ገና ከመነሻው በተዋንያን አማካኝነት በመድረክ ላይ የሚደረስ በመሆኑ ከሌሎች በአያለው የተለየ ነው፡፡

## 2.1.2 የትውፊታዊ ተውኔት ምንነት

ትውፊት ማለት ካለፈው ትውልድ ወደሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፍ ዘመናትን ያስቆጠረ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖር ስርዓት ነው፡፡ ትውፊት አንድ የማህበረሰቡ መገለጫ ከመሆኑ የተነሳ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በሙሉ የትውፊት አካል ናቸው፡፡ የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት አኗኗር ውስጥ የተለያዩ ክብረ ባዓላትን በሚያከብርበት ጊዜ የሚያከናውኗቸው ክንውኖች ምን እንደሚመስሉ፣ እንዴት እንደሆኑ እና በማን እንደሚከወኑ ለትውልድ የሚያስተላልፍበት መንገድ ነው፡፡ ትውፊት ማለት የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ያከናወናቸው ረጅምና ውስብስብ የሆነ ታሪካዊ ክስተትና የፈጠራ ውጤቶች ድምር ነው፡፡ ስለትውፊት የተለያዩ ጸሀፊዎች የተለያየ ስያሜ ይሰጣሉ፡፡ ፈንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገባ ቃላትና ቢያኔዎቻቸው ከሀ-ፐ" በተሰኘው መጽሀፍ ላይ እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡

> *"ትውፊት ከአለፈው ዘመን ወይም ከአለፈው ትውልድ የተወረሰና ዘመነኛ ደራሲዎች በጥናትና በምርምር የሚማሩትን እምነት፣ ስነ ቃል፣ አስተሳሰብ እና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ ጸሀፊ ተውኔቱም ሆነ ሌላው ደራሲ ለፈጠራ ስራዎች በቀጥታ የሚገለገልባቸው የትውፊት አይነቶች በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ከአላፊው ትውልድ የወረሳቸውን እንደ ቋንቋ፣ ስነ ጽሁፋዊ ዘውጎችና ደንቦች፣ አካላዊና ቁሳዊ እንዲሁም መንፈሳዊ ባህሎች የመሳሰሉ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ትውፊት የሚለው ቃል የሚፈጠር ሳይሆን የሚወርሱትን የሚያመለክት ነው፡፡" (1993፣ 59)*

ትውፊታዊ ተውኔት አንድን ማህበረሰብ ትውፊት ቀድቶ ትያትራዊ ቅርጽ አስዞ መድረክ ላይ የሚቀርብ ሲሆን አቀራረቡም ከተውኔት አላባዊያን በአለፈ የማህበረሰቡን ባህልና ዕሴት በጠበቀ መልኩ የመኪቀርብ የተውኔት አይነት ነው፡፡ ትውፊታዊ ተውኔት የማህበረሰቡን ባህል ለሚቀጥለው ትውልድ ወይም ባህሉን ለማያውቀው ሰው ትውፊቱን በማስተማር ረገድ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ይህም ትውፊት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍበት አንዱ ክፍል ነው፡፡

## 2.1.3 የትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን

ትውፊታዊ ተውኔት የራሱ የሆነ መገለጫ ወይንም ዓላባዎያን አሉት፡፡ ስለ ትውፊታው ተውኔት አላባዊያን አዲስ አለም አስቻለው "ንግስት ዘውዲቱ ታሪካዊ ተውኔት " በሚለው

መጽሀፉ ላይ እንደሚከተለው አስቀምጧል፡፡ እነሱም መቼት፣ ቃለ ተውነት፣ አልባሳት፣ ታሪክ፣ ሚናክፍፍል፣ ቁሳቁስ ናቸው፡፡(2010፣3) ዓ.ም፡፡

### 2.1.3.1 መቼት

መቼት ማለት አንድ ድርጊት የሚከወንበት ወይንም የሚፈጸምበት ቦታና ጊዜን የሚገልጽ፣ ተውኔቱ ወይም ድርጊቱ በየትኛው ቦታና ጊዜ እንዲሁም ሰዓት እንደተፈጸመ ወይም እንደተከወነ የምናውቅበት አንዱ የተውኔት ክፍል ነው፡፡ ፋንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው ከሀ-ፐ" በተሰኘው መጽሀፍ እንሚከተለው ገልጿል፡፡

> *"መቼት መቼትን የሚያሰኙው የ ድርጊቱ ጊዜ፣ ቦታ እና ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ያለው ማህበራዊ እውነታ ናቸው፡፡ መቼት አጠቃላይ መቼትና ውስን መቼት በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡ አጠቃላይ መቼት በአንድ በተወሰነ የተውኔት ድርሰት ውስጥ የሚገኘው ትልቁ ድርጊት መከወኛ፣የጊዜ መለኪያ እና ትልቁ የድርጊት መከወኛ ቦታ ነው፡፡ ውስን መቼት ደግሞ በአንድ በተወሰነ የተውኔት ድርሰት ውስጥ የሚገኘው ትንሹ የድርጊቱ መከወኛ ቦታና ትንሹ የድርጊት ጊዜ ነው"፡፡ (1999፣11) ዓ.ም፡፡*

በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ መከናወኛ ቦታ መቼት የሚለውን ተውኔት አላባዉያንን ይወክላል፡፡ መቼት የአንድ ተውኔት ፣ልብወለድ፣ የግጥምና የፊልም ታሪክ የሚከናወንበት ቦታ፣ ጊዜና ማህበራዊ እውነታ ነው፡፡ መቼት "መቼ" እና "የት" የሚሉትን ቃላት የያዘ ሲሆን ትርጉሙም ተውኔታዊ ጊዜው የሚከናወንበት ቦታና ጊዜ ያመለከተናል፡፡

ይህም መከወኛ ቦታ ማለት ትውፊቱ የሚከወንበት ቦታ እና ጊዜ በማጠቃለል ይይዝልናል፡፡መቼት የአንድ ማህበረሰብን የአኗኗር ሁኔታ ጠቋሚ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ የበጋ፣ የክረምት ጊዜያትን ግልፅ ያደርጋል፡፡ በደራሲው እንደሚያከናውኑት ድርጊት ትክክለኛ የማህበረሰቡ ባህላዊ ክንውኖች ባህሉ ያለውን ተጨባጭ የሆነ የጋብቻ ስነ-ስርአቶች፣ የቀብር ስነ-ስርአቶች፣ የአምልኮ ሁኔታዎች ማህበረሰቡ በሚከናወኑ መንገድ ይቀርባሉ፡፡ ሳሙኤል ተስፋዬ‹‹የመድረክ ጆርባ ጥበባት›› በተሰኘው መፅሀፍ ስለ መቼት እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

*መቼት የተውኔት ታሪክ የሚከናወንበት ቦታናታሪኩ የሚከወንበት ጊዜንና ማህበራዊ እውነታንአጠቃልሎ የያዘዘ ነው። አብዛኛው ፀሀፊተውኔቶች ተውኔታቸውንመፃፍ ሲጀምሩ የሚያስቀድሙት ነገር የታሪኩን ቦታና ጊዜማህበራዊ እውነታን በማስተዋወቅ ነው። ይህ ደራሲው የሚሰጠን አለም አብዛኛውን ጊዜ ከምናውቀው ገሀድ አለም የተመሳሰለ ነው። (2012፣131)*

መቼት ጠቃሚና በተውኔት ውስጥ ጉልህ ሚና ያለው ሲሆን በፀሀፊ ተውኔት ታሪክ ውስጥ አጠቃላይ፣ ውስን፣ የጊዜ፣ የቦታ ማህበራዊ እውነታን በአንድ ላይ አካቶ የያዘ ነው። በአጠቃላይ መቼት ውስጥ ደራሲው በፈጠራው ታሪክ ውስጥ ያለው ትልቁ የድርጊቱ መከወኛ ቦታ ነው። ሀገር፣ ዘመን፣ የፖለቲካሁኔታ፣ ሀይማኖታዊ ስርአትን ያጠቃልላል። በውስን መቼት ውስጥ በደራሲው ታሪክ ውስጥ ባሉ አነስተኛ የቦታና የጊዜ ሁኔታ ማህበራዊ እውነታን ጨምሮ የያዘ ነው።

### 2.1.3.2 ቃለ-ተውኔት

ቃለ ተውኔት አንድ እና ከዚያ በላይ በሆኑት ከዋኞች መካከል የሚደረግ ንግግር ሲሆን በአንድ ተውኔት ውስጥ ጭብጥ፣ መቼት፣ ሴራ፣ ታሪክ ምን እንደሁነ የሚያሳዉቅ የተዉኔት አላባውያን ነዉ። የገጸ ባህሪያትን ማንነት ማለትም አመለካከትን ወይም አስተሳሰብን፣ የኑሮ ደረጃን ወዘተ የምናውቅበት ወይም የምንረዳበት መንገድ ነው። ደበበ ሠይፉ "ከጸሐፌ ተዉኔቱ አንጻር " በሚለው መጽሀፍ ላይ እንደሚከተለው አስቀምጧል።

*"የተዉኔት ቋንቋ ከገጸባህርያቱ አንደበት እሚዉጣዉ ቃለ ተዉኔት ነው። ቃለ ተዉኔት በሁለት እና ከዚያ በበለጡ ሰዎች መሀል የሚደረግ ንግግር ወይም ዉይይት(ዉይይቱ እጅግ የናሩ ግጭቶችን የያዘ ሊሆን ይችላል) ነው። ቃለ ተዉኔት ቁጥብነት ያለዉ ሴራዉን ወደ ፊት የሚያራመድ ነገር መሆን አለበት"።(1973፣40)*

ቃለ ተዉኔት በትዉፊቱ ላይ ከሚሳተፈዉ ሰዉ የሚወጣ ንግግር ነዉ ። ቃለ ተዉኔት በስዎች የሚደርግ እና ሲራዉን ሊያራመድ የሚችል ነዉ ። በተጨማሪ ዘሪሁን አስፋዉ "የስነጽሁፍ መሰረታውያን"በሚለዉ መጸሃፍ እንዲህ ይላል።

*"ምልልስ በዘዴነቱ የገጸ+ባህሪትን ስሜት፣ አላማ ፣ ችግር እንዲሁም ስነ ልቦናዊ መልክ ማሳያ ነዉ። ተሳታፊ ገፀ ባህሪያት ያላቸዉን ግኑኙነት ለማሳወቅ ይጠቅማል። በገፀ ባህሪያት መካከል የሚደረገዉ ምልልስ ለምልልስነቱ ወይም ሁለቱ ገፀ ባህሪያት ንግግር እንዲለዋወጡ ብቻ ለማድረግ የሚፈጠር አይደለም"።(2004፣205)*

ገጸ ባህሪያት በተውኔት ውስጥ በሚፈጠሩት ተውኔታዊ ቋንቋ የእርስ በእርስ ግንኙነታውን ከመግለጽ በተጨማሪ ስለ ተውኔቱ ምንነትና ለማስተላለፍ ተፈለገውን ሀሳብ ተመልካች በቀላሉ እንዲረዳ ያደርጋል። ቃለ ተውኔት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው። የገጸ ባህሪያቱ የንሮ ደረጃ የስራ ድርሻ፣ ውስጣዊ አስተሳሰብ፣ የተሳሉበት መንገድ፣ ማህበራዊ መስተጋብራቸውን በተውኔት ውስጥ በስፋት ያሳያል።ይህ ማለት በከዋኞች መካከል የሚደረገው ንግግር ከሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ቡድኖች የሚደረግ ሲሆን የከዋኞች ማንነት እና ሚና እንዲሁም ታሪክ የሚገልፅ ነው።

በተጨማሪ ሳሙኤልተስፋዬ "የመድረክ ጀርባ ጥበባት "በሚል ርዕስ ባሳተመው መፅሀፍ ላይ ስለ ቃለ-ተውኔት የሚከተለውን አስፍሯል።

*"ቃለ ተውኔት የገፀ ባህሪውን ውስጣዊና ውጫዊ ማንነት ፣ ግልፅ እና ድብቅ ስብእናውን ፣ ሀይማኖቱን ፣ ፍልስፍናውን ፣ሸንፈቱን ፣ድክመቱን ፣ ብርታቱን ድሉን የየት ሀገር ሰው እንደሆነ ምን አይነት አለባበስ እንደሚያዘወትርየስራውን አይነት ማህበራዊ ደረጃውን ባህሉን ወግልማዱን ወዘተ በቃለ ተውኔት ውስጥ ልናገኛቸው እንችላለን" ።(2012 ፣ 197)*

ገፀ-ባህሪያት በተውኔት ውስጥ በሚፈጥሩት ተውኔታዊ ቋንቋ የእርስ በእርስ ግንኙነታቸውን ከመግለፅ በተጨማሪ ስራ ተውኔቱ ምንነትእና ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ

ተመልካች በቀላሉ እንደረዳ ያደርጋል፡፡ ቃለ- ተውኔት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አለው፡፡ የገፀ-ባህሪያቱን የኑሮ ደረጃ፣ የስራ ድርሻ፣ ውስጣዊ አስተሳሰብ፣ የተሳሉበትን መንገድ፣ ማህበራዊ መስተጋብራቸውን በተውኔት ውስጥ ያሳያል ፡፡

### 2.1.3.3 ቁሳቁስ

ቁሳቁስ ማለት የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር የሚገለገልባቸው ወይም የሚጠቀምባቸው እንደየአይነታቸው የተለያየ ጥቅም የሚሰጡ መሳሪያ ናቸው፡፡ ቁሳቁስ በሰው ህይወት ውስጥ በጣም አስፈላጊ እንደመሆኑ ሁሉ በትያትርም አስፈላጊነታቸው የጎላ ነው፡፡ ቁሳቁስ በአንድተውኔት ውስጥ የተለያዩ ማለትም ማህበራዊ ሁኔታን፣ ጊዜን እና ገጸ ባህሪያትን ማንነት እንድናውቅ ይረዳናል፡፡ *ሳሙኤል ተስፋዬ "የመድረክ ጀርባ ጥበባት"* በሚለዉ መጸሃፍ እንዲህ ይላል፡፡ "*ቁሳቁስ በዕይታ ዉስጥ እጅግ ገዢ የሆነ ሚና ሊጫውቱ ይችላሉ፡፡( 2012 ፣ 121)*

በሌላ በኩል ደግሞ ፋንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ቢያኔዎቻቸው ከሀ-ፐ " በሚለው መጽሀፍ ውስጥ ስለ ቁሳቁስ አይነቶች እንደሚከተለው አስፍሯል፡፡

> *ቁሳቁስ አራት ክፍሎች አሉት፡፡ በአንደኛ ደረጃ የመድረክ ቁስ የሚባሉት ተዋኒያን መድረክ ላይ በእጃቸው ላይ የሚይዟቸው እንደ ደብዳቤ፣ ብርጭቆ፣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የመድረክ ትይንቱ አካል በመሆን የሚቀርቡ እንደመቀመጫ ወንበር፣ አልጋ፣ ቁምሳጥን፣ ማቀዝቀዣ የመሳሰሉት እንዲሁም የመድረክ ቁሳቁስ ይባላሉ፡፡ ከዚህ ሌላ የግርግዳ ጌጦች ለምሳሌ እንደሚለጠፉ ስዕሎች፣ የመስኮት መጋረጃዎች፣ ግድግዳ መስታዎቶች እና የመሳሰሉትም መድረክ ቁሳቁስ ናቸው፡፡ (1993፣85)*

ቁሳቁስ ማንኛውም አይነት ቁስ ሆኖ ለዬትኛውም ክዋኔ የተለየ ጥቅምን የሚሰጥ ሊሆን ይችላል፡፡ የሰው ልጅ ሲንቀሳቀስ ወይም ሲቀመጥ ቁሳቁስን ይጠቅማል፡፡

### 2.1.3.4. አልባሳት

አልባሳት በአንድ ተውኔት ውስጥ ያሉ ገጸ ባህሪያት በመደረክ ላይ ሲተውኑ የሚለብሱት ልብስ ነው፡፡ ስለ አልባሳት ፋንታሁነ እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት ከሀ-ፐ" በሚለው መጽሃፉ ላይ እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡፡

*"አልባሳት ተዋኒያን ዝግጅታቸውን በመድረክ ላይ ለህዝብ በሚያቀርቡ ጊዜ የሚለብሱት ልብስ መጠሪያ ነው። አልባሳት የሚለው ቃል የመጣው ምንጩ ከቤተክርስቲያን ነው። ቀሳውስት፣ ጳጳሳት እና ዲያቆናት በክብረ በዓላትና ለስራተ ቅዳሴ ወደ ቤተ መቅደስ በሚገቡ ጊዜ የሚለብሱትን ልብስ እና የሚዘረጉትን ዣንጥላ ይጨምራል። አልባሳት ጊዜን፣ ቦታን፣ የኑሮ ደረጃን፣ እምነትን፣ ጾታንና የሚያ መስክን፣ ግላዊ ጸባዩንና የንቃተ ህሊናን ደረጃ ሳይቀር ሊወክሉ ወይም ሊጠቀሙ ይችላሉ"። (1993፡2)*

አልባሳት በትውፊታው ተውኔት ውስጥ የገጸ ባህሪያትን ማንነት እንዲሁም በሚቀርበው ተውኔት ውስጥ የኑሮ ደረጃን፣ የወደፊት ተስፋን፣ ፍቅርን፣ አብሮነትን መግለጽ ይችላል። በተጨማሪ ሳሙኤል ተስፋዬ ‹‹ የመድረክ ጀርባ ጥበባት›› በሚለው መፅሀፍ ውስጥ ስለ አልባሳት የሚከተለውን አስፍሯል።

*"በቲአትር ጥበብ ውስጥ አልባሳትሰፊ ትርጉም የያዘ ጥበብ ሆኖ እናገኘዋለን ።በመሆኑም አልባሳት የምንላቸው ሁሉምየሚለበሱ ነገሮችን አጠቃሎ የያዘ ሲሆንተዋንያንሽሽ ከውስጥ የሚለብሷቸው ልብሶከላይ የሚደርቧቸው ልብሶች ፀጉራቸው ላይ የሚያስሯቸው ሻሾች፣ አንገታቸው ላይ የሚያደርጉት ስካርቭ ትክሻቸው ላይ ጣል የሚያደርጉትሻርፕ(ነጠላ)፣ ጋቢ በራሳቸው ላይ የሚያደርጉትክፍያዎች፣ ዘውዶች ፣ አክሊሎች፣ ቆቦች፣ጥምጣሞች፣እና መሰል ነገሮች በሙሉ አልባሳት ዝርዝር ውስጥ ይመደባሉ"። (2012፣ 100)*

አልባሳት በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ የገፀ-ባህሪያቱን ማነት እንዲሁም በሚቀርበው ተውኔት ውስጥ የኑሮ ደረጃን ፣ የወደፊት ተስፋን ፣ ፍቅርን ፣ ክብርን መግለፅ ይችላል ።

### 2.1.3.5 ታሪክ

ታሪክ ያለፈ ዘመንን አጥርቶ የሚያሳይና ዛሬ ላይ ያለንበትን እንድንገነዘብ ያደርጋል። ፋንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ቢያኔዎቻቸው ከሀ-ፐ" በሚለው መጽሀፋ ላይ ስለታሪክ እንዲህ ይላል።

*“ማንኛውም ተውኔታዊ ድርጊት ወይንም ክንዋኔ በጊዜ ቅደም ተከተል ተዘርዝሮ የሚቀመጥ ነው። ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል መሰረት ከአንዱ ድርጊት ቀጥሎ የትኛው ድርጊት እንደሚከተለው ለማሳወቅ ይጠቅማል። ታሪክ የክዋኔዎች ስብስብ በመሆኑ ለማንኛዉም የፈጠራ ስራ ማለትም ለተውኔት፣ ለረጅም ልበወለድ፣ ለአጭር ልበወለድ፣ ለፊልም፣ ለተራኪ ግጥም እና ልዩ ልዩ ተረቶች መሰረት ነው ተብሎ ይታመናል”። (1993፡55)*

ታሪክ በተውኔታው ተውኔት ውስጥ የአንድ ብሄረሰብ ባህል የሚያጎላ ስለብሄረሰቡ መለያ በመሆን የማንነት መግለጫ ሆኖ ያገለግላል። በሌላ በኩል ደግሞ ዘርሁን አስፋው “የስነ ጽሁፍ መሰረታዊያን” በተሰኘው መጽሐፉ ታሪክን በሚገባው ያብራራል።

*“ታሪክ በተወሰነ የጊዜ ቅደም ተከተል የተቀናጁ ሁኔቶች ትረካ ነው። ታሪክ የአንድ ጊዜውን ጠብቆ የሚቆይ ትረካ ነው። የጊዝውን ቅድመ ተከተልን ያልጠበቀ ከሆነ ግን ታሪኩ መዘበራረቅ .... ስለሚዘበራረቅ ድርሰቱም ተውነቱም የተዘበራረቀ ይሆናል ማለት ነው”።(2004፡156)*

ታሪክ በተውኔት ውስጥ የድርጊት ቅደም ተከተልን ጠቋሚ ነው። በተውኔት ውስጥ እና በሌሎች የስነ-ፅሁፍ ዘርፎች፣ ልቦለድ ፣ወግ፣ ፊልም ውስጥ ታሪክ መሰረታዊ አላባ ሆኖ ይገኛል። ታሪክ በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ የአንድ ብሔረሰብ ባህል የሚያጎላ ለብሔረሰቡ መለያ በመሆን የማንነት መግለጫ ሆኖ ያገለግላል። ታሪክን ለማወቅ እና ወደ ተውኔት ለመቀየር የታሪኩ ባለቤት ጋር በመቅረብ ታሪክ አዋቂዎችን በመጠየቅ ጥናዊ ፅሁፎችን፣ መፃህፍትን በማንበብ ማወቅ ይችላል። ታሪኩ ለተውኔት ሲቀርብ ብሔረሰቡ ሊቀበለው የሚችል ያልተዛባ ቅደም ተከተልን ያዘለመሆን አለበት። ታሪክ በተውኔት ውስጥ ድርጊቶችን በማከል የነገሮችን ትክክለኝነት እና ትክክል ያልሆኑትን ይለያል።

## 2.1.3.6 ሚና ክፍፍል

ሚና ክፍፍል ማለት የስራ ድርሻ ማለት ሲሆን በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ የቤተሰብ አባላት የራሳቸው የሆነ የስራ ክፍፍል ወይም ድርሻ እንዳላቸው ሁሉ በአንድ ተውኔት ሆነ በሌላም ስራ ላይ ያሉ ሰዎች ወይም ተሳታፊዎች ስራውን ለማቅለል ወይም ጊዜ

ለመቆጠብ የየራሳቸውን የስራ ክፍፍል ወይም ድርሻ በመያዝ በአግባቡ ለመወጣት አስፈላጊ ነው፡፡ ፋንታሁን እንግዳ "ተውኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ቢያኔዎቻቸው ከሀ-ፐ" በተሰኘው መጽሀፋ ላይ እንደሚከተለው አስፍሯል፡

> *"ተዋንያን የሚጫወቱበት ድርሻ ነው፡፡ የሰው ልጅ በዕለታው ህይወት የሚወጣው ሚናና ተዋኒያን በመድረክ ላይ የሚተውኑት ሚና ተብሎ በሁለት አብይ ክፍል ሊካፈል ይችላል፡፡ በአጠቃላይ የመድረክ የትወና ሚና ታስቦበት ተጠንቶ ለመቅረቡ ተዋንያኑም ተመልካቹም የሚረዳ ጉዳይ ሲሆን የማህበረሰባዊና ግለሰባዊ ሚናዎች በእያንዳንዱ ግለሰብ የመድረክ ወይም የመቀፀል ችሎታ የሚወሰን ይሆናል"፡፡(1993፡29)*

በሌላ በኩል ደግሞ ፒተር ሃሮፕ እና አቦነህ አሻግሬ (1984,12)፣ A preliminary investigation of dramatic element with in Traditional cerimonies, በተሰኘው መፅሀፍ ውስጥ እንዲህ ሲል ይገልጽዋል፡፡

> *"የሚና ክፍፍል የምንለው በትውፊታዊ ተውኔት ክንውን ውስጥ የድርጊት፣ የቃለ ምልልስ፣ ወዘተ መሰል ልዩነቶችን ያካትታል፡፡ በከዋኞች መካከል ያሉ ክፍፍሎችን በውስጡ ያያዘ ሲሆን ከዋኞች ያላቸውን የስራ ድርሻ፤ የከዋኞች ሚናን በድርጊትም ሆነ በቃለ ምልልሰ በትውፊቱ ውስጥ የሚወጡትን ድርሻ ይይዛል በማለት ይገልጹታል"፡፡ (1984,12)*

ይህም ከዋኞች የሚከውኑት ክዋኔ ውስጥ ያላቸውን ወይም የሚወጡትን የስራ ድርሻ ወይም የድርጊት ክፍፍል ነው፡፡ በቃለ ተዉኔት ከዋኞች በሚከውኑበት ወቅት እንደ ሚናቸው የሚናገሩት ንግግሮችም የሚና ክፍፍላቸውን ሊገልፅልን ይችላል ማለት ነው፡፡ በትውፊታዊ ተውኔት የሚና አከፋፈል ድርጊቱን በሚከውኑ ኩነቶች ከባህሉ ባለቤት ከሆኑት የማህበረሰቡ አባላት ጋር የሚኖረው የተውኔት ጊዜ ዕድሜን፣ ጾታን፣ ሀይማኖትን፣ ግላዊ አስተሳሰብን፣ የእውቀት ደረጃን ባማከለ መልኩ ያቀርባል፡፡ በትውፊታዊ ተውኔት የሚሳተፉ ተዋንያን ተውኔት ውስጥ ባላቸው ተሳትፎ መጠን ድርሻን ይወስዳሉ፡፡

## *2.1.4 ሰርግ ምንነት*

ሰዎች በትዳር ለመኖር ህወታቸውን ለመምራት ሲሉ የሚያደርጉት አብሮ መኖር ስምምነት ሆኖ ቤተሰቦቻቸው፣ ቤተዘመድ፣ ጎረቤት፣ አከባቢ ነዋር በሙሉ ገጽታዉን የሚገልጽበት ወላጆችም ራሳቸውን ለማዝናናት በእምነታቸው መሰረት ልጃቸውን ድረው ለማፅረግ የሚያበቁበት እና ለማህበረሰቡ የእወቁልኝ ፕሮግራም የሚያዘጋጁበት ተጋቢዎች ከአንድ የህይወት ምዕራፍ ወደ ሌላ የህይወት ምዕራፍ መሸጋገራቸውን የሚያበስሩበት ስርዓት ነው፡፡ ካሳየ ገብረ እግዚአብሔር "ባህልና ክርስቲነዊ ትውፊት በኢትዮጲያ " በሚለው መጽሀፉ ላይ ሰርግን እንደሚከተለው ገልጾታል፡፡ *ሰርግ ከጥሎሽ ቀጥሎ የሚመጣ የጋብቻ አንዱ ክፍል ነው፡፡ የሰርግ ጥሬ ትርጉሙ ጋብቻ፣ በዓል፣ ድግስ፣ የሚያጌጡበት፣ የሚሸለሙበት ማለት ነው፡፡ ለሰርግ ህይወታቸውን መሰረት የሚጥሉበት፣ እናት አባታቸውን ትተው እርስ በእርሳቸው አንድ የሚሆኑበት ልዩ የደስታ ቀን ነው፡፡ (1972፣99)*

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ሰርግ ሁለቱ ተጋቢዎች የወደፊት የአንድነት የንሮ ምዕራፋቸውን በመጀመር ከእናትና አባታቸው ጉያ ወቶ በራሳቸው ለመወሰን፣ ራሳቸውን ለመምራት፣ አባት እናት ለመሆን እና የልጅ ባለቤት ለመሆን የሚያዘጋጁበትን ለወገን ዘመድ የሚያሳውቁበት የደስታ ቀን ነው፡፡ መጽሐፈ ቅዱስም እንዲህ ይላል፡፡ *"እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ ባረካቸው ብዙ ተባዙ የባህርንም ውሃ ሙሏት ወፎችም በምድር ላይ ይብዙ፤ ላባም የዚያን ስፍራ ሰዎች ሰብስቦ ሰርግ አደረጉ፡"* ዘፍ /29፡22/ ሲል ይገልጸዋል፡

## *2.2 የተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፎች ቅኝት*

አጥኚው ጥናታዊ ጽሁፍን የሚያጠና በምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነስርአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን አንጻር ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸውን ጥናታዊ ፅሁፎች እንደ ተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝትነት ተጠቅሟል፡፡ ሰዋየሁ ለገሰ በ2010 ዓ.ም በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቲአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ‹‹ የኦሮሞ ጉጂ የጋብቻ ስነ-ስርአት ከቃለ-ተውኔት እና ከመቼት አንፃር›› በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው ፡፡ የሰዋየሁ ለገሰ ጥናታዊ ፅሁፍ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች የጋብቻ ስነ ስረአቶች ላይ ማተኮራቸው እና ባህላዊ ስረአቶች ላይ ትኩረት በማድረጋቸው ያመሳስላቸዋል ፡፡ የሰዋየሁ ለገሰ ጥናታዊ ፅሁፍ እና ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚለያያቸው ነገር ደግሞ የሰዋየሁ ለገሰ ጥናት የጉጂ ኦሮሞ የጋብቻ ስነስርዓት ከቃለ

ተውኔት ከመቼት አንፃር ነው ። በዚህም መሰረት ሁለቱ ጥናቶች በርዕስ እና መረጃዎችን የሚተነትኑበት መንገድ ይለያያል ።

በሌላ በኩል ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያለዉ በትዉፊታዊ ተዉኔት ላይ የተሰራ በምድራዊት እንዳለ በ2013 ዓ.ም በወልቂጤ ዩንቨርሲት የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል " የሀሩ የቡሄ በዓል አከባበር ከትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን አንጻር" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው።  ምድራዊት እንዳለ በጥናቷ ስለ ሀሩ የቡሄ በአል አከባበር በትውፊታው ተውኔት አላባዊያን አንጻር በሚል ርዕስ በአራት ምዕራፎች ክፋፍላ ጥናታዊ ጸሁፋን አቅርባዋለች።

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ከምድራዊትቭ እነዳለ ጽሁፍ ጋር የሚመሳሰለው ትውፊታዊ ተውኔትን መስረት አድርገው ባህላዊ የሆኑ ስነስራአቶችን በማተኮራቸውና ሁለቱም በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ በሚከበረው ባህላዊ ስነስርአቶች ላይ ትኩረት ማድረጋቸው ነው። ይህ ጥናት ከምድራዊት እንዳለ ጥናታዊ ጽሁፍ ጋር የሚያለያያቸው ሁለቱም በተለያዩ ማህበረሰቦች ላይ ጥናታቸውን ማድረጋቸው በተጨማሪም ከርዕስ ጀምሮ የሚያጠናው ባህልና መረጃን የሚተነትኑበት መንገድ ይለያያል።

በተጨማሪ በ2011 ዓ.ም መቅደስ ሞገስ በወልቂጤ ዩንቨርሲት የትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለባችለር ኦፍ አርት ዲግር ማሟያነት "የፈጫሳ አምልኮ ስርአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባዊያን አንጻር" በሚል ርዕስ የተሰራ ጥናታዊ ጽሁፍ ሲሆን በውስጡም አራት ምዕራፎች አሉት።ይህ ጥናታዊ ጹሁፍ ከመቅደስ ሞገስ ጋር የሚያመሳስላቸዉ ሁለቱም ጥናቱች ከትውፊታው ተውኔት አላባዊያን አንጻር መተንተናቸዉ ነዉ። ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ከመቅደስ ሞገስ ጥናት የሚያለያያቸዉ  ሰሜን ሸዋ ዞን በምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ሲሆን ይሄ ጥናት ግን በምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሃን ወረዳ በመሆኑ ሁለቱ ጥናቶች የተለያዩ ማህበረሰብ ላይ የተደረጉ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም የመቅደስ ሞገስ ጥናት የሚያጠናው የአምልኮ ስርአት በመሆኑ ይህ ጥናት ግን የሚያተኩረው የሰርግ ስነስርአት ላይ ነው።

## ምዕራፍ ሶስት

## 3. የመረጃ ትንተና

### 3.1 የፈለገ ብርሃን ወረዳ መልካ ምድራዊ ዳራ

የፈለገ ብርሃን ወረዳ በአማራ ክልላዊ መንግስት ዉስጥ ጎጃም ላይ የሚገኝ ሲሆን የጉጃም ማህበረስብ በሁለት ዞኖች ተከፍሎ ይኖራል፡፡ ዞኖችም ምስራቅ ጉጃም እና ምራዕብ ጎጃም ዞን በመባል ይታወቃሉ፡፡ በምራዕብ ጎጃም ዞን 17 ወረዳ ሲኖሩ በምስራቅ ጉጃም ዞን ደግሞ17 ወረዳዎች፣5 የከተማ መስተዳድር ይገኛሉ፡፡ ከእነሱም ዉስጥ የፈለገ ብርሃን ወረዳ አንዱ ነዉ፡፡ የፈለገ ብርሃን ወረዳ በሚኖርበት አካባቢ በድንበር የሚዋሰኑት ሌሎች ክልሎች እና ዞኖች ይገኛሉ፡፡ በምስራቅ ደቡብ ወሎ ዞን፣ በምዕራብ ምዕራብ ጎጃም እና አዊ ዞን፣ በሰሜን ጎንደር እና ትግራይ ክልል፣ በደቡብ የኦሮሚያ ክልል ያዋስኑታል፡፡ የፈለገ ብርሃን ወረዳ የገቢ ምንጭ የሆነው እና ህዝቡ ራሱን የሚያስተዳድረው ፣ በእርሻ በቆሎ፣ድንች፣ስንዴ፣ ገብስ እና ጤፍ በስፋት በማምረት ፣ የቀንድ ከብት እርባታ ፍየል ላምና በሬ በማርባት ፣ የዶሮ እርባታ ፣ ንብ ማነብ ፣ ንግድ ፣ እንስሳትን በማድለብ እና በመሸጥ ኑሮውን ይገፋል፡፡ የፈለገ ብርሃን ወረዳ ህዝብ ህይወቱን በመሰረተበት በአማራ ክልል ቆላ ፣ ደጋ ፣ ወይናደጋ ፣ የአየር ንብረት አለው፡፡ የማህበረሰቡ የስራ ቋንቋ አማረኛ ብቻ ሲሆን የራሱ የሆኑ የአለባበስ የአመጋገብና የተለያዩ ስነስረዓቱች ያሉ ሲሆን ከነዚህ መካከል የሰርግ ስነስረአት አንዱ ነዉ፡፡

## *3.2 የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነረዓት ክንዉን*

የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት ክንዉን ምን ይመስላል?ብለን በጠየቅናቸዉ መሰረት መምህር አለሙ ሰዉነት ክንዉኑን ከዚህ በታች እንዲህ ይገልጡታል። የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነ ስረዓት ከመካሄዱ በፊት ቅድመ ክንዉን አለዉ። በመጀመሪያ የወንዱ ቤተሰቦች 3-5 ሽማግሌዎችን ወደ ሴቷ ቤተሰብ ይልካሉ። ሽማግሌዎች ከሄዱ በሆላ ሰላምታ ይለዋወጣሉ። ከቤት ዉጭ(አዳሬ)ነጭ አጎዛ ይነጠፍላችዋል። ሽማግሌዎችም ጋቤያቸዉን አጣፍተዉ ይቆማሉ። ከዚያም በሆላ የሴቷ ቤተሰቦች ወይም አባት ምን ፈልጋችሁ ነዉ ብለዉ ይጠይቃሉ።ከዚህ በመቀጠል አባት ሁኑን ልጅ እንሁናችሁ (ልጃችሁን ለልጃችን ብለዉ ጥያቂ ያቀርባሉ። ከዚህ በሆላ የወንድ ቤተሰብ እጅ ነስተዉ ጉልበት ይስማሉ። ከሳሙ በሁላ ወደ ነጭ አጎዛ መቀመጫዉ እንዲቀመጡ ይደረጋል መሪት ንኩ ይባላል። ከዚህ በሁላ ወደ ቤት ይገቡና ግብዣ ይደርግላቸዋል። ግብዣዉ ካበቃ በሁላ የሰርጉን ቀን ለመዉሰን በሌላ ቀን ቀጠሮ ይዘዉ ይለያያሉ። በሌላኛዉ ቀን የሙሽሮች ቤተሰቦች እና ሽማግሌዎች ተገናኝተዉ ቀን ይቆርጣሉ። ይህ የቅጥር ቀን ይባላል። የቅጥር ቀኑ ከተቆረጠ በሁላ የሙሽሮች እናት እና አባት የወንድ ቅጥር እና የሴት ቅጥር በመባል ዉል ይይዛሉ።

በመቀጠል የሰርጎ ቀን ሙሽራዉ ሁለት ሚዜዎችን የሰርጉ ዋዜማ ማታ ሁለት በጎችን በመጨመር ወደ ሴቷ ቤተሰቦች ይዘዉ ይሄዳል።በጎች የእጅ መንሻ ይባላሉ። ማታ በሴቷ ቤተሰቦች ዘንድ ዘመድ አዝማድ ይሰበሰብና ከወንድ ቤተሰብ የተላኩትን በጎች በሚዜወች አማካኝነት ርክክብ ይካሄዳል። በርክክብ ስነ ስረዓቱ ላይ ከበጎች በተጨማሪ ጥሎሽ ይሰጣል 50 ብር ለእናት ጉያ 20 ብር ለሚሚ በ አጠቃላይ 200 እና ከዛ በላይ ወጭ ይደርጋል። ከተከፈለ በሆላ ሚዜዎች ከቤተ ዘመዱ ጋር ተቀላቅለዉ ከተዘጋጀዉ ድግስ (ሌማት)ይበላሉ። ከበሉ በሁላ ቤተዘመዱ በሆታ ወደቤት ሲገቡ አብረዉ ይገባሉ። ከገቡ በሁላ ሲጫወቱ አምሽተዉ (ሲደልቁን ሲፎክሮ አምሽተዉ) ወደ ሙሽራዉ ቤት ይመለሳሉ።

በሰርጉ ቀን ሙሽራዉ እና ሠርገኙችን በመጨመር 25-30 ሰዎችን በመያዝ ይሔዳሉ። ሁለት ፈረስ በመጨመር ከሄዱ በሁላ ወደ ሙሽሪት ቤት ሲደርሱ የተቀመጡትን ሽማግሌዎች እጅ በመንሳት ከተዘጋጀላችሁዉ ቦታ ይቀመጣሉ። ከዚያ በሁላ ሠርገኛ ለብቻዉ ሌማት ይሠጠዋል። የሙሽራዉ የቅርብ ጓደኙች እና ሚዜዎች ለብችሃችሁዉ ጫጉላ ይቀመጣሉ። ለእነሱ የሚሆን ጠላ ሚዜዎች በመሄድ ከሙሽሪት ቤት በመቅመስ ጥሩ ነዉ ያሉትን ጠላን አርቂ በመምርጥ ለሙሽራዉ ያመጣሉ። የተዘጋጀዉን ምግብና መጠጥ እየበሉና እየጠጡ ጨዋታ ይጫወታሉ።

ቤተዘመድ ሌማት በልቶ ከጨረስ በሓላ ወደቤት ይገቡና ጨዋታ ይጫወታሉ። ቤተዘመድ ከተጫወተ በሁላ ለጨዋታ የተመርጠ ሚዜወች ወደ ቤት ይገቡና እያረፎ ሶስት ጊዜ እንዲደልቆ ይደረጋል። ከዚህ በሁላ ከቤት ወጥተዉ ወደ ነበሩበት ቦታ ይቀመጣሉ። በሰርጉ ዋዜማ የሄዱት ሚዜዎች ድንኳኖ(እዳሱ) ላይ ወደ ተቀመጡት ሽማግሌዎች በመሄድ ለሙሽሪት ያመጡትን ሻሽ(ባዉንድ)፣ ቀሚስ፣ ጥላ፣ ሱሪ፣ ካባ፣ ጫማ እና ባርኔጣ ቆጥረዉ ያስረክባሉ። በመቀጠል ከሴቷ ቤተሰብ የወከለ ሠዉ የሴቷን ልብስ ማለትም ቤተሠቦች የገዙለትን ልብስ፣ ቀሚስ፣ ኩታ፣ ጫማ፣ ሻሽ፣ አገልግል፣ ሙዳይ፣ ሳጥንና ጀንዲ ለሚዜወች ያስረክባሉ። ሚዜወችም የተረከቡትን እቃ ይዘዉ ወደ ሠርገኛዉ ይሄዱና ለሰርገኛዉ አከፋፍለዉ ይሰጣሉ።

የሴት ቤተሰብ ደግሞ ከሚዜወች የተረከቡትን አልባሳት በመዉሰድ ለሙሽሪት እንድትለብሰዉ ይደረጋል። ከዚህ በሁላ በግምት ከምሽቱ 4-5ሠዓት አካባቢ ሙሽሪት ከቤተሰቦቿ ቤት ትወጣለች። ሙሽሪት ከበር ስትወጣ አባቷ በመጀመሪያ ጥይት ይተኩሳል። በመቀጠል የቅርብ ዘመዶቿ አብረዉ ይተኩሳሉ። ከዚህ በሗላ ሙሽረዋ ከቤት እስከ ሽማግሌዎች ድረስ ከሚዜዎች(ሰርገኞች)ዉስጥ አንዱ ያላገባዉ ተመርጡ ያደርሳታል። ከዚያ በሗላ ለጉዞ በተዘጋጀዉ ፈረስ ላይ ወስዱ ይሰቅላታል። ከሠቀላት በሁላ ሙሽሪት ከፈረሱ ላይ ተቀምጣ የሙሽሪት ዘመዶች ፎከራና ቅራርቶ ይጫወታሉ። ጨዋተዉ ካለቀ በሁላ በሃገር ሽማግሌዎች ተመርቀዉ ሚዜዉችና ሙሽራዉ ጉልበት ይስማሉ። የሽማግሌዎችንና የቤተሰቦቿን ጉልበት ከሳሙ በሁላ ሰርገኛና ሚዜ አቅራርቶ፣ ፎክሮ ሙሽራይትን ይዞ ወደ ሙሽራዉ ቤት ይሄዳሉ።

በግምት ከምሽቱ 7-8 ሠዓት በሚሆንበት ከወንድ ሙሽራ ቤት ይደርሳሉ። ከደረሱ በሗላ በእልልታና በሆታ የሙሽራው ዘመድ አዝማድ ይቀበላቸዋል። ከዚህ በሁላ ወደ ሙሽራዉ ቤተሰቦች ቤት አንድ የበግ ግልገል ሙሽራዉ ካረደ በሗላ የታረደዉን በግ በመራመድ ሙሽራውና ሙሽሪት አጃቢዎችን ጨምሮ ወደ ቤት ይገባሉ። ከገቡ በሁላ የሙሽራዉ ሚዜዎችና ዘመድ አዝማድ ለተወሰነ ግዚ ጨዋታ ይጫወታሎ። ከዚህ በሗላ የሙሽራዉ የቅርብ ጓደኙች /ሚዜዎች ሙሽሮችን ከቤት አስወጥተዉ ከቤቱ አጠገብ ከተሰራዉ ለሙሽራዉ ማደሪያ ቤት(ጫጉላ)ይገባሉ። ከገቡ በሁላ ከሁለት ሚዜ ጋር ሙሽሮች ጫጉላ ገብተዉ ያድራሉ። በሶስተኛዉ ቀን ወደ ሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት ከ6-7 ሚዜዎችን በመጨመር ሙሽሮችን ወደ ሙሽሪት ቤት ይዘዉ ይሄዳሉ። ሴቷ ሙሽራ በፈርስ ተሰቅላ ካባ፣ሻሽና ባርኔጣ ወንዱ ሙሽራ ደግሞ ወንጨሪ ሱሪ በመልበስ ይሄዳሉ። ከሙሽራዉ ቤት አንድ በግ አብሮ

ተይዙ ይሄዳል፡፡ እሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት ከሄዱ በኋላ ሙሽራዉ እና ሙሽሪት ከቤት ዉጭ ተቀምጠዉ አብረዉ የሄዱ ሚዜዉችህ ለሁለት በመከፈል ከሙሽራዋ ቤተሰቦች ዉስጥ ይገባሉ፡፡

የሙሽረዋ ቤተሰብ ዘመድ አዝማድ እቤት ዉስጥ ፊታቸዉን በመሸፈን የተወሠነ ክፍተት በአይን ብቻ በመተዉ ይቀመጣሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ሚዜዎች ሻሽ፣ ፎጣ እና አታሞ በመያዝ ወደ ቤት ዉስጥ ገብተዉ ወሶወሶ ባሮ ወንድሜ ቀናወይ እያሉ በመዝፈን እና አታሞ በመምታት የሙሽሪት እናትና አባት ፍለጋ የጀምራሎ፡፡ የሙሽሪት እናት ወይም አባት ናቸዉ ብለዉ የሚጠረጥሯቸዉን ሰዎች ላይ ፎጣ ወይም ሻሽ አንገታቸዉ ላይ አስረዉ እየዘፈኑ ተገለጡ ብለዉ ያዝዛሎ፡፡ ሻሽ ወይም ፎጣ የተደረገላቸዉ ሰዎች እንዲገለጡ ይታዘዛሉ፡፡ የተገለቱት ሰዎች እናት ወይም አባት ካልሆኑ የተደረገላቸዉን ፎጣ ወይም ሻሽ ለብሰዉ ይቀመጣሉ፡፡ የሙሽሪት ቤተሰቦች በፍለጋ እስከሚገኙ ድረስ የሚዜዎች አልባሳት እሰከሚያልቅ ድረስ እየዘፈኑ ይፈልጋሉ፡፡

በመጨረሻም የሙሽሪት ቤተሰቦች እናት ወይም አባት ሣይገኙ ከቀሩ እና የሚዜዎች አልባሳት ካለቀ እንደተሸነፉ ለመግለጥ አንድ ልብስ እቤቱ ምሠሶ ላይ ያስራሉ፡፡ ካሰሩ በኋላ የጠፉት እናት ወይም አባት የሚያሳይ ከሙሽሪት ቤተዘመድ አንድ ሰዉ ይመረጣል፡፡ የሙሽራዉ ሚዜዎች እንደ ቤተዘመድ ይቀመጡ እና ከቤተዘመድ የተመረጠዉ ግለሰብ የጠፉትን የሙሽሪት ቤተሰቦች ትክሻ ላይ ጋቢ፣ ሻሽ ወይም ፎጣ ያስቀምጣል፡፡ እናት እና አባት ከተገኙ በሁላ የደስ ደስ ሚዜዎች ይደልቃሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል የሰርጉ ዋዜማ የተሰጠዉን ብር ለመመለስ ሚዜዎች ይቁማሉ፡፡ ደስ ብሉናል ደስ ይበላቹህ ብለዉ ለቤተዘመዱ ደስታ ያበስራሉ፡፡ የሙሽሪት ቤተሰቡችም እንኳን አብሮ ደስ አለን የሚል ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ በመቀጠል የአደራ ገንዘብ አለን ይመለስልን ይላሉ፡፡ ለማን እንደሰጡ ይጠየቃሉ፡፡ የሰጡትን ግለሰብ ስም ይጠራሉ፡፡ ግለሰቡም ለጥሉሽ ለማሚ ተብሉ የተከፈለዉን ብር ይመልሳል፡፡ በመቀጠልም መልሰዉ በአደራ ለግለሰቡ ይሰጣሉ፡፡

ከዚያም ወደ እዳሪ (ዉጭ) ይወጡና ከሙሽራዉ ቤተሰብ የመጣዉን በግ ሙሽራዉ በማረድ ተራምደዉት ወደ ቤት ይገባሉ፡፡ ሚዜዎችም የታረደዉን በግ ይገፉና ስጋዉን በቁጥርና በአይነት ለሙሽሪት ቤተሰብ ያስረክባሉ፡፡ እቤት ከገቡ በኋላ የሚበላና የሚጠጣ ከቀመሱ ቅራርቱና ፉከራ ይንሳል፡፡ በመጀመሪያ ሚዜዎች ይፎክራሉ ፡፡ በመቀጠል ሙሽራዉ ይነሳ እና ይፉክራል፡፡ የሙሽሪት ቤተሰቦች እንደያቅማቸው ለሙሽራዉ ይሸልማሉ፡፡ ጨዋታዉ እና ሽልማቱ ካለቀ በኋላ ይተኛሉ፡፡ በማግስቱ ማታ ያረዷትን በግ ያስቀርቡና ለሁለት እኩል ይከፍሉና ግማሹን ለሙሽሪት ቤተሰቦች  ይሰጣሉ፡፡ ግማሹን ደግሞ ለሙሽሩች እና ለሚዜዉች

ይዘጋጅላቸዋል። እየበሉ እየጠጡ ከዋሉ በኋላ በግምት ከቀኑ ከ10-12 ሠዓት ተመልሰዉ ወደ ሙሽራዉ ቤተሰብ ይሄዳሉ። ወደ ሙሽራዉ ቤት ቀጥታ ይገቡና ከዘመድ አዝማድ ጋር ሲጨዋወቱ ያመሻሉ። በግምት 4-5 ሠዓት ዘመዱ ወጥቶ ወደ መኖሪያ ቤቱ ይሂዳል። ሙሽሩች ከሙሽራዉ ቤተሰብ ጋር አብረዉ ያድራሉ።

ከዚህ በሗላ ለአርባ ቀን ይጠበቃሉ። ብቻቸዉን እንዳይንቀሳቀሱ ለእያንዳንዳቸዉ ሙሽሩች ሰዉ ይመደብላቸዋል። ከአርባ ቀን በሗላ የሙሽሪት ቤተሰቦች እንደ አቅማቸዉ በግ በመግዛት ወይም በማዘጋጀት ምላሽ ይጠራሉ። ሙሽራዉ እና ሙሽሪት አንድ ሚዜ በመያዝ እሙሽሪት ቤተሰቦች ላይ ይሄዳሉ። ሚዜዉ አላማጅ ይባላል። የተዘጋጀዉ በግ ከታረደ በኒላ አንድ ቀን በመቆየት ወደ ቤቱ ይመለሳል። ሙሽሮች ከ3-5 ቀን ይቆያሉ። ከዚያ በኒላ ወደ ሙሽራዉ ቤተሰቦች ተመልሰዉ አብረዉ መኖር ይጀምራሉ።   ሲሉ ተናግረዋል።(መምህር አለሙ ሰዉነት ፣ 20/06/2015 ዓ.ም)

## *3.3 "የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት ከትዉፊታዊ ተዉኔት አላባዉያን አንፃር"*

### *3.3.1 መቼት*

መቼት ማለት ቦታ ጊዜና ማህበራዊ እውነታ በውስጡ የያዘ የተውኔት አላባ ነው። የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነስርዓት የተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ያለው ሰርግ ነው።አብዛኛውን ጊዜ የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነስርዓት የሚከወነው በጥር እና በሚያዚያ(የፋሲካ ሰሞን)የሚካሄድ ነው። ይኸውም የሚሆንበት ምክንያት በዚህ ወር ማህበረሰቡ አንድ ማህበራዊ እውነታ አለው። ይኸውም በዚህ ወር ወይም ወቅት እህል (ሰብል) የሚደርስበት ወቅት በመሆኑ ነው። ሰርግ ለመሰረግ እህል እና ሌሎች ወጪዎች የሚወጡበት ማለትም ለእርድ የሚያስፈልጉ ከብቱች እንዲሁም የፍስክ ሰሞን ስለሆነ  ወቅቱ ተመራጭ ወር ነው።

አንድ ቤተሰብ ሰርግ ለመሰረግ ቢያንስ 6 እና ከዛ በላይ ኩንታል ጤፍ (የእንጀራ እህል) ያስፈልገዋል። እንዲሁም ሌሎች ወጪዎች ይኖራሉ። ታድያ ሰርግ ለመሰረግ ያሰበ ቤተሰብ ሰብል የሚደርስበትን የጥር ወር ወይም በሚያዚያ(የፋሲካ ሰሞን) መጠበቅ ግዴታው ነው። አንድም እህሉን ለሰርጉ እንጀራ ሊጠቀሙበት ሁለት ደግሞ  አውጥቶ ወደ ገበያ በመሸጥ በምትኩ ዘይት እና ለሰርግ የሚያስፈልጉትን ቅመማ ቅመሞች ለመግዛት ነዉ። በዚህም

ምክንያት የጥር ና የሚያዚያ ወር ለዚህ የሰርግ ስነስርዓት በማህበርሰቡ ዘንድ ተመራጭ ወቅት ነው።

ሰርጉ የሚደረግበት ቦታ በሁለቱም ማለትም በሙሽረዋ ቤተሰብ እና በሙሽራዉ ቤተሰብ ነዉ። የሴቷ ቤተሰብ ማለትም የልጁ እና የልጅቱ ቤተሰብ ለጋብቻ ከተስማሙ የመጀመሪያው ግብዣ የሚሆነው በልጅት ቤተሰብ ቤት ነው። የዚህም ምክንያት የልጅት ቤተሰብ ለሽማግሌዎች ያላቸውን ከበሬታ ለመግለፅ፣ በተጨማሪ ወንዱ ሙሽራ ሚዜወችን ይዙ በመሄድ ሙሽረዋን ካመጣ በሁላ  በእነሱ ቤት የሚካሄድ ነዉ። ምላሽ በማለት ልጁን እና ቤተሰቡን በቤታቸው መጥራት ደግሞ ከዚህ በኂላ ባዳ(ባዕድ) አለመሆናቸውን እና አንድ መሆናቸውን ለማመልከትም ጭምር ነው። በዚህ በልጅቱ ቤተሰብ ቤት የሚሆነው ግብዣ ከሰአት ከ6፡30 ጀምሩ ነው። ምክንያቱም ብዙ ሰዉ ምሳ የሚበላበት ሰዓት ስለሆነ እና ሰርጉ እንዲደምቅ በተጨማሪ የአስራጊዉን(የደጋሹ) ስም ለማስጠራት የሚደረግ ግብዣ ስለሆነ ለመዘገጃጀት እና ለግብዣው የሚያስፈልገውን ሁሉንም ነገር በዕለቱ ጠዋት ስለሚያከናውኑ ነው።ከግብዣው በኂላ ሁለቱም ቤተሰብ ለሰርጉ መዘገጃጀት ይጀምራሉ።

## *3.3.2 ቃለ- ተዉኔት*

ቃለ ተዉኔት የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት እንደ ቃለ-ተውኔት ወይም ንግግር የሚወሰደው ምርቃት፣ ዘፈኖች እና ተማፅኖ ነው።  ይህንንም የምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሃን ወረዳ  የሰርግ ስነ ስረዓት ወቅት ስንመለከት፤ በሰርግ ስነስርዓት ሂደት ውስጥ የተለያዩ ምልልሶች አሉ። ይህንንም በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተዘጋጀው ያልታተመ ፅሁፍ ሲገልፅ፡-

‹‹ የሴት ቤተሰብ፡- ግቡ እንጂ ?

ሽማግሌዎች፡- የለም አንገባም ።

የሴት ቤተሰብ፡- ምነው.... በደህና ?

ሽማግሌዋች፡- አዎ በደህና ነው። ...አመጣጣችንም እንዲህ ነው አባት ትሆኑን ዘንድ እኛም ልጅ ልንሆናችሁ መተናል።.....ልጃችሁን ለልጃችን ስንል መጣን ።

የሴቷ ቤተሰቦች፡-ልጃችሁን ለልጃችን ስትሉ ማነው?----ለማን ብላችሁ ነው?

ሽማግሌዎች፡-እከሊትን ለእገሌ አባባሉ ልጅ,

የሴት ቤተሰብ፡- የገሌ አባባሉ ልጅ የማነው ልጅ? ትውልዱስ የት ነው?

ልጁስ እንዴት ነው? ይጠይቃሉ፡፡

ሽማግሌዎች፡- ትውልዱ ፈለገ ብርሃን እዚሁ ፈለገ ነው ፣ ልጁም

የተዋጣለት ገበሬ ነው፡፡ ዘሩም፣ ትውልዱም የእኛው ነው

ብለን ነው የመጣነው››

በማለት በሽማግሌዎች እና በሙሽሪት ቤተሰብ መካከል የሚደረጉት ምልልሶች ከቅድመ ሰርግ ሁኔታ ላይ መመልከት በሌላ በኩል በሰርጉ ላይ የሚዚሙ ግጥማዊ ሙዚቁች እና ምርቃቱች ፣ ፍኩሩች፣ ቅራርቱዉች በሙሉ ቃለ ተዉኔት ይጠቀማል፡፡ የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነስረዓት ላይ ሚዚዎች የሚዘፍኑት ዘፈን በግጥም ከዚህ በታች ተቀምጧል፡፡

ሙሽሪት ለምዳለች፣
ሙሽሪት ለምዳለች፣
እንዝርቴን ደጋጌን ላኩለኝ ብላለች፣
ላኩለኝ ብላለች፡፡

የኛ ሙሽራ ሱሪ መጀብ(2 ጊዜ)
ከእንግዲህ ቀረ መደባደብ፡፡
የኛ ሙሽራ ኩሪባቸዉ ፣
ኩሪባቸዉ፣
በእንግሊዝ አናግሪያቸዉ፡፡
እንዳላይሽ እንዳላይሽ ፣
ዳመናዉ ጥሏል በበላይሽ፡፡
ጡረዉ ጡረዉ አማጭህን፣
ጡረዉ አማጭህን፣
ከዚች ቆንጆ ያጋባህን፣
ጡረዉ አማጭህን፡፡
የኛ ሙሽራ ሹራብ ሰሪ፣

ሹራብ ሰሪ፣

ወሰዳት አስተማሪ።

በማለት ያዜማሉ እንዲሁም እንዲህ እያሉ ይፉክራሉ።

ዘራፍ አጅሪ ዘራፍ አጅሪ

የሙሽር ወንድም ወንድም ወንድሙ

አይገመግምም ያልፋል በደሙ ።

እንኳን ሙሽራዉ አይዙህ እያለው

እንኳን ሙሽሪት አይዙህ እያለችው

እንደዉም ልጁ ጥጋበኛ ነዉ።

ሀምሳ ቢወለድ ሀምሳ ነዉ ጉዱ

የሙሽር ወንድም ይበቃል አንዱ።

ገና ሲነሳ ነፍሱን አያዉቀዉ

ቅዱስ ሚካኤል አንተ ጠብቀዉ። በማለት ይፉክራሉ።(መምህር ክፍሌ ሽፈራዉ፣

20/06/2015ዓ.ም)

ይህም ለቃለ ተዉኔት የምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነ ስረዓት ውስጥ ማሳያ ነው።

### 3.3.3 ቁሳቁስ

ቁሳቁስ የሰው ልጆች በየ እለት ተእለት ክንውናቸው የሚጠቀሙባቸው ረዳት አገልጋዮች ናቸው። ቁስቁሶች የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት ውስጥ አገልግሎት ይሰጣሉ። የፈለገ ብርሃን የጋብቻ ስነ-ስርአት በሚከወንበት ጊዜ ቁሳቁሶች ከግልጋሎት ባለፈ መልዕክቶችን ያስተላልፋሉ። አጥኚው የፈለገ ብርሃን የጋብቻ ስነ-ስርአት ላይ በተመለከተው መሰረት የቁሳቁሱን ሚና እንደሚከተለው አስፍሯል።

ጀንዲ(ቆዳ):(ጀንዲ) ወይም ቆዳ በመባል የሚታወቀው ከሰንጋ በሬ ታርዶ የሚገፈፍ ቆዳ ነው። ይህ ቆዳ ከታረደው በሬ ከተገፈፈ በኋላ ቆዳ በሚፍቁ(በቆዳ ሰራተኛ) ሰዎች ተፍቆ ለመኝታ እንዲያገለግል ተደርጎ ይሰራል። ይህ ቆዳ ሙሽሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ጫጉላ ቤት ውስጥ አብረው የሚተኙበት ነው። ጫጉላ ለሁለቱ ሙሽሮች የሚዘጋጅ ትንሽዬ ቤት ሲሆን

ከላይ ገለባ (የባህር ዛፍ ቅጠል)፣ ግድግዳውን በትልልቅ ሳር (በድርቁሽ) ነው የሚሰሩት፡፡ጥሩ ሽታ ያላቸውን ቅጠላ ቅጠልም በ ጫጉላ ቤት ውስጥ ይገባሉ ምክንያቱም የቆዳዉ ሽታ ስላለዉ ሽታዉን ለማጥፋት ነዉ። ይህ ቆዳም እዚሁ ጫጉላ ቤት ውስጥ ከስር ቅጠል ከተረበረበ በኂላ ቆዳውን ከላይ ያደርጉበታል፡፡

ሙሽሪት እና ሙሽራውም እዚህ ጫጉላ ቤት ውስጥ የመጀመሪያ ግንኙነታቸውን ያደርጋሉ። ይህ ቆዳ እና ጫጉላ ቤት ምን ትውፊታዊ ትርጓሜ ይሰጣል ብለን የ አካባቢዉን ተወላጅ መምህር አለሙ ሰዉነት ስንጥይቅ። "እንዲህ ብለዉ መልሰዉልናል። ጫጉላዉ መሰራቱ የሚጠቅመዉ ሙሽሪት እና ሙሽራዉ የመጀመሪያ ግንኙነት የሚያደርጉ በጫጉላ ነዉ። አንድ ሚዜ አብሩ ይኖራል። እሱም የጭን ሚዜ በመባል ይጠራል። የጭን ሚዜ ስራዉ ወንዱ ሙሽራ ከሴቷ ሙሽራ ጋር ግብረ ስጋ ግኑኝነት በሚያደርግበት ወቅት ለማድረግ ከከበደዉ(ሴቷ ካስቸገርች) የሙሽሪት ጭን በመክፈት ለሙሽራዉ አጋዥ ይሆናል። የጭን ሚዜ የሚሆነዉ የተመረጠ ሰዉ ነዉ። እሱም የሙሽራዉ የቅርብ ዘመድ መሆን አለበት ምክንያቱም በጫጉላ ዉስጥ ብዙ ነገር ሊፈጠር ይችላል። ለምሳሌ የሙሽረዋ ክብረ ንፅህና ላይገኝ ይችላል ወይም ደግሞ ወንዱ ሙሽራ ወሲብ ላይ ሰነፍ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በማህበርሰቡ ዘንድ አስነዋሪ ነገር ስለሆነ ከቤተሰብ ዉጭ ይህንን ነገር ሌላ ሰዉ እንዲያየዉ አይመከርም" ብለዉ መልሰዉልናል። በመቀጠልም በጫጉላ ቤት ዉስጥ ቆዳ (ጀንዲ) ለምን አስፈለገ ብለን በጠየቅናቸዉ መሰርት እንዲ ብለዋል። ቆዳ(ጀንዲ) ለሙሽራው ምቾት እንዳይሰማውና እንቅልፍ እንዳይወስደው ነው፡፡ ምክንያቱም ቀኑን ሙሉ በጭፍራ እና ወዲህ ወድያ እያሉ ስለሚውሉ የተመቻቸ ፍራሽ ካገኘሙሽራው ስራውን ዘንግቶ ሊያንቀላፋ ይችላል፡፡ እናም ሙሽራውን የሙሽሪትን ክብረ ንፅህና መውሰድ አለበት፡፡ ይህን ማድረግ ካቃተው ሙሽሪት ትታው መሄድ ትችላለች፡፡ ለዚህም ነው ሙሽራው እንቅልፍ እንዳይጥለው በጫጉላ ቤት ውስጥ ቆዳ ላይ መተኛት ያለበት፡፡" በማለት ነግረውናል፡፡(መምህር አለሙ ሰዉነት፣ 20/06/2015ዓ.ም)

መሶብ ወርቅ( አገልግል) "ከስንደዱ እና ከግራምጣ በወስፌ የምትስራ ስትሆን ሙሽሪት ወደ ሙሽራዉ ቤት ስትሄድ በጀርበዋ አዝላት የምትሄድ ትንሽየ አገልግል ናት፡፡በዉስጡም መድፌ፣ምላጭ፣ፊት የምታሳይ ትንሽ መስታየት፣ወስፊና ዳቦ ቆሎ ትይዛለች። ሙሽሪት ባለሙያ መሆኖን እና በጫጉላ ዉስጥ ለሚያስፈልጋት ማንኛዉ ነገር አማቶቹን ሳታስቸገር በራሷ ለመወጣት እንዲያስችላት ነዉ፡፡ማለትም ለቤቱ አዲስ ስለሆነች አይን አዉጣ ልጅ ናት ብለዉ አማቱቿ እንዳያሰቡት እና አማቱቿን ለመጠየቅ ስለምታፍር ነዉ። ወስፊ የምትይዝበት

ምክንያት ደግሞ በወስፌ አማካኝነት ብዙ ነገር ይሰራል:: ወስፌ አንዱ የሙያ መለኪያ መንገድ ነዉ:: ለምሳሌ ሞሰብ፣ወስከባይ፣ ቆለምሸሽ እና ሙሽሪት ወደ ሙሽራዉ ቤት ይዘዉ የምትመጣዉ ሞሰብ ወርቅ(አገልግል) በወስፌ አማካኝነት የሚሰሩ ቁሳቁሶች ናቸዉ:: ሙሽሪት በአማቱቿ ቤት ባለሙያናት እና ያመጣችዉን መሶብ ወርቅ (አገልግል) እሷ መስራቷን ማረጋገጫም ነዉ::" በማለት የማህበርሰቡ ነዋሪ ወይዘሮ ብርቱካን ይበልጣል ተናግረዋል:: (ወይዘሮ ብርቱካን ይበልጣል፣ 20/06/2015ዓ.ም )

ዋንጫ:- ይህ ከከብቶች ቀንድ የሚሰራ ለመጠጫ የሚያገለግል እቃ ነው፡፡ በባለሞያ ከቀንድ የሚሰራው ይህ ዋንጫ ሙሽሮች የሚቀርብላቸውን መጠጥ የሚጠጡበት ነው፡፡ በማህበረሰቡ ዘንድ ይህ እቃ ትልቅ ክብር ያለው በመሆኑ ሙሽሮች በዚህ እቃ ይጠቀማሉ፡፡ መመገቢያ ሰሃኔ፣ እንስራ ፣ ሰፌድ፣ ብረትድስት፣ ሳጥን፣ ጠረጴዛ፣ ጆክ፣ እና የመሳሰሉት ቁሳቁሶች በዕለቱ ሰርግ ላይ ለሙሽሮች በስጦታ መልኩ የሚመጡ ናቸው፡፡፡ ሙሽሮች ጎጆ ወጪ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ የተለያዩ ቁሳቁሶች በስጦታ መልኩ ይሰጣሉ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ የሰርግ ስነ-ስርዓት ላይ ያሉት ቁሳቁሶች ትውፊታዊ ይዞታ ያላቸው እና በማህበረሰቡ ዘንድም አሁን ላይ እየተረሱ መሆኑን ወይዘሮ ብርቱካን ይበልጣል ባደረግንላቸው ቃለ-መጠየቅ መሰረት ነግረውናል፡፡

### *3.3.4 ግብአተ ድምፅ*

የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት ላይ ግብአት ድምፆች አገልግሉት ላይ ይዉላሉ:፡፡ በጋብቻ ስነ-ስርአቱ ላይ ባህላዊ የሆኑ የማጀቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ሰርጉን ያጅባሉ፡፡ መምህር ክፍሌ ሽፈራዉ የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት የግብአት ድምፅ ሚናን እንደሚከተለው ያስረዳል ::"ለሰርጉ ማጀቢያ የሚያገለግሉ የባህላዊ ሙዚቃ መሳሪያዎች በአቅራቢያ የሚገኙ ጡሩምባ፣ የመሳሪያ ተኩስ ፣ ማሲንቁ ፣ ጭብጨባ፣ አነስተኛ ከበሮ በአንድ እጅ በመምታት ለሰርግ ማጀቢያ ይጠቀማሉ::(መምህር ክፍሌ ሽፈራዉ፣ 20/06/2015ዓ.ም)

ወንዶች ጎን ለጎን በመሆን አልያም ክብ ሆነው በመጨፈር፣ በማቅራራት ፣ ጡርንባ እየነፉ የሚወጣውን ድምፅ እንደ ማጀቢያ በመጠቀም ይጨፍራሉ:: ሴቶች እጃቸውን ወደ ግራ ቀኝ እያወዛወዙ በመሀል እያጨበጨቡ እንዲሆም በእልልታ ሰርጉን ያደምቁታል፡፡

## 3.3.5 አልባሳት

አልባሳት የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት ላይ የአልባሳት ሚና ሰውነትን ከመሸፈን በተጨማሪ የክብር፣ የጋብቻ ፣የወደፊት ምኞትን፣ የኑሮ ደረጃን ይገልፃል፡፡ አቶ ሙሉቀን ሽፈራዉ የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት ላይ ያላቸውን ሚና እንደሚከተለዉ ይገልፀዋል፡፡ "የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ሰነ ስረዓት ላይ ወደ ሴቷ ቤት የሚያቀና ሙሽራ ከሙሽራዉ አንስቶ እስከ ሰርገኞቹ የተለያየ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ ሙሽራው የሚለብሰው ሙሉ ሱፍ ሲሆን፣ ሱፍ ከጉልበቱ ወረደ ይልና ከስር ሰፋ የሚል ሱሪ ነው፡፡ ጫማው ቆዳ በመባል የሚታወቅ ሲሆን የጫማው መልክ ሙሉ ለሙሉ ነጭ ነው፡፡ ይህ ጫማ ትንሽ ተረከዝ ያለው ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በማህበረሰቡ ውስጥ ብዙም አይስተዋልም፡፡ ሙሽራው ፀጉር ካለው ጎፈሬ ካለዉ ይስተካክል እና ለሰርጉ ይዘጋጃል፡፡ ሚዜዎቹ ደግሞ ተመሳሳይ አይነት አለባበስ ሆኖ ከሙሽራው በመልኩ የሚለይ ነው፡፡ ለምሳሌ የሙሽራው ሱፍ ነጭ ከሆነ የሚዜዎቹ ደግሞ ጥቁር ይሆናል፡፡

ሙሽሪት ደግሞ ከጥጥ ፈትል የሚሰራ ሙሉ ነጭ ቀሚስ ትለብሳለች፡፡ የምትጫማው ጫማ ልክ እንደ ሙሽራው ሁሉ ነጭ ሲሆን ቆዳ ፣ጎማ ፣ወይም ሸራ ጫማ ሊሆን ይችላል፡፡ ሙሽሪት ፀጉሯን ወደ ኋላ አበጥራ ማስያዝ፣ አልያም ደግሞ ፀጉሯን በባህላዊ መልኩ መሰራት ትችላለች፡፡ የሙሽሪት እና የሙሽራው ቤተሰብ የፈለጉትን አይነት ልብስ መልበስ አይችሉም ወንዱች ሱፍ በቆዳ ጫማ ያደርጋሉ፡፡ የሱፉ ከለር የሚፈልጉትን አይነት መልበስ ይችላሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን ደግሞ አባት ሙሉ  ነጭ ይለብስና ጋቢ ከላይ ይደርባል፡፡ እናቱች ደግሞ ነጭ ሙሉ ቀሚስ በመከንት አስረዉ በሽፍን ጫማ ያደርጋሉ፡፡ ሰርገኞች በበኩላቸው የተሰፋ ሙሉ ሱሪ ይለብሳሉ፡፡ ሌሎች በሰርጉ ላይ ተጠርተው የሚታደሙ ታዳሚዎች የፈለጉትን የልብስ አይነት ለብሰው መታደም ይችላሉ፡፡" ሲሉ  ይገልጡታል፡፡

ሙሽሪት እና ሙሽራው ለምን ከስር እስከ ላይ ነጭ መልክ ያለው ልብስ እንደሚለብሱ **አቶ ሙሉቀን** ሽፈራዉ ባደረግንላቸው ቃለ-መጠይቅ እንዲህ ያወጋሉ፡፡ ‹‹ ሙሽሪት እና ሙሽራው ነጭ የሚለብሱት እስከ ሰርጉ ዕለት እራሳቸውን ጠብቀው ስለቆዩ በተለይ ሙሽሪት ጋብቻው መጀመሪያዋ ከሆነ ክብሯን ጠብቃ እስከ ጋብቻዋ በመኖሯ ንፅህነዋን ለመግለፅ እና ለማመልከት ነው፡፡ ነጭ ንፅህናን ይወክላልና፡፡ ሙሽራው ነጭ መልበሱ ያን ያህል ላይሆን ይችላል፡፡ ብቻ ለሙሽራውም ቢሆን ትርጉሙ አንድ አይነት ነው፡፡

በተጨማሪም የምላሽ ደግሞ የምትለብሰዉ አለባበስ  የተሰፋ ልብስ ክላዩ ካባ ትለብሳለች ። ወንዱ ሙሽራም እንድዚዉ ወንጨሪ ሱሪ እና ከላይ ካባ  ይደርባል።ሲሉ ተናግረዋል።(አቶ ሙሉቀን አስራቴ ፣20/06/2015ዓ.ም)

ሙሽራውም የሙሽሪትን ቤተሰብ ስያለብስ (ለሙሽሪት አባት ጋቢ ለእናቷ ደግሞ ነጠላ ወይም ቀሚስ ይሰጣቸዋል። ለሙሽሪት በዕለቱ በሰርጉ ላይ የሚታደሙ ዘመድ እና ወዳጆቹ ነጠላ እና ሌሎች አልባሳትን በስጦታ መልኩ ሊሰጧት ይችላሉ።

### 3.3.6 ሚና ክፍፍል

የምስራቅ ጎጃም ዞን የፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነ ስረዓት ውስጥ ከጅማሬው ጀምሮ እስከ ፍፃሜው ድረስ ባለው ሂደት ውስጥ የተለያዩ የስራ ድርሻዎችን በመውሰድ ይሰራሉ። ይህንንም የፈለገ ብርሃን ወረዳ የአማረኛ መምህር የሆኑት መምህር ስንታየዉ ሽፈራዉ እንዲህ ይገልጻሉ፡-

‹‹ ማህበረሰቡ፡- ሰርጉ ሲደገስ ወጪ በማጣት፣ጠላ በመጥመቅ፣
እንጀራ በመጋገር፣ወጥ በመስራት፣ የሰርጉን
ዳስ ማዘጋጀት፣ስረአቱን መታደምን ይተገብራሉ።
የወንድ ቤተሰብ፡- ለሙሽሮች የሚሆን ቤት የሚጨጎሉበትን
ማዘጋጀት፣ ሙሽሮችን መሸለም። ድግሱን መደገስ።
የሴት ቤተሰብ፡- ሰርጉን መዘጋጀት፣ ሽልመት መዘጋጀት፣
ስጦታዎችን መስጠት፣ የወንድ ቤተሰብን መሸለም።
የስር ሚዜ፡- ሙሽሮችን መንከባከብ፣ ገበያ በመሄድ ሎሚ
መግዛት፣ አገዳ መግዛት፣ ሙሽሮች በሚጨጎሉበት
ወቅት የሙሽሮችን ቤተሰብ ለአርባ ቀን እንደ ልጅ
ሆኖ የቤት ውስጥ ስራን መስራት።
የሙሽሪት ክርስትና እናት፡- ለቃል ማሰርያ የሚሰጠውን ብር
በመቀበል ከራሷ ገንዘብ በመጨመር ለሙሽሪት

ስጦታ መግዛትና በስርጉ እለት መሸለም፡፡

ሽማግሌዎች፡- ልጅህን ለልጃችን መማፀን፣ስርጉን ማስተባበር፣

ሙሽሮችን መመረቅ፣ እስከ ሰርግ ፍፃሜ ድረስ

ያለውን ክዋኔ መከታተል፡፡

እናቶች፡- ሙሽሮች ሲወጡ መዝፈን፡፡››

በማለት እያንዳንዳቸውን ክዋኔ በመተንትን ገልፀዋል፡፡ በዚህም መልኩ እያንዳንዳቸው ከዋኞች ከታዳሚው ጀምሮ የሚያደርጉትን ስራ የሚና ክፍፍል በማረግ የሰርግ ስነ ስረዓቱን ይከውናሉ፡፡(መምህር ስንታየዉ ሽፈራዉ ፣20/06/2015ዓ.ም)

## ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሃሳቦች

### 4.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት ትኩረቱን ያደረገው በአማራ ክልል፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን፣ በፈለገ ብርሃን ወረዳ ውስጥ በሚከወነው የሰርግ ስነስርአት ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር መተንተን ላይ ነው፡፡ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሰርግ ስነ ስረዓትን ከትውፊታዊ ተውኔት አላባውያን አንፃር ምን እንደሚመስል እና ያለውን ተዛማጅነተ ለመቃኘት ሞክሯል፡፡ ይህ የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነ ስረአት በዚህ ምስራቅ ጎጃም ዞን አከባቢ ለሚኖሩ ማሕበረሰብ የላቀ እና ተወዳጅነት ያለው የሰርግ ስነ ስረአት መሆኑን አጥኚው ከአጠናው ጥናት መረዳት ችሏል፡፡ይህ የፈለገ ብርሃን የጋብቻ ስነ ስረአት በሚከወንበት ወቅት ማሕበረሰቡ ትውፊታዊ ድረጊቶችን በመጠቀም ስለፍቅር፣ስለትዳርና ስለቃልኪዳን የመሳሰሉት መልክቶችን በተለያየ መንገድ ሲያስተላልፍ ኖሯል፡፡ ለምሳሌ፡በሚለብሱት አልባሳት፣በሚጠቀሙበት ቁሳቁስ ፣በፎከራ ፣ በምርቃቶች እና ንግግሮች እና በመሳሰሉት መንገድ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፍ ኖሯል፡፡ አሁን ላይ ግን ይህ ስርዓት እንደ ዘመናዊነት፣ ትኩረት ባለመሰጠቱ እንዲሁም

ቻልተኝነት በመሳሰሉት ስነ ስርዓቶች እየተረሳ መምጣቱን አጥኚው ከአነጋገራቸው የማሕበረሰቡ አካላት በጥናቱ ለማረጋገጥ ችሏል።ይህ ጥናታዊ ፅሁፍበአማራ ክልል፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን፣ በፈለገ ብርሃን ወረዳ ውስጥ በሚከወነው የሰርግ ስነስርአት በምን መልኩ እንደሚካሄድ ፣ በማን እንደሚካሄድ ፣ የሚካሄድበት ቦታ (መቼት) ፣ አልባሳት ፣ ቁሳቁስ ፣ ግብአተ ድምፅ ፣ ድርጊት ፣የሚና ክፍፍልን ፣ በባህሉ ውስጥ ስነስርዓቱ እንዴት በትውፊታዊ ተውኔት ላይ እንደሚውል ለማሳየት ሞክሯል ። በፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነስርዓት በክዋኔው ሂደት ውስጥ የመከወኛ ቦታ (መቼት) ፣ የተመረጠበት ምክንያት የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነስረአት ላይ ሴት ልጅ በዉንዱ ቤት መኑር ስላለባት ነዉ ተብሉይጠቁማል። አልባሳት የወንድም የሴት በሰርግ ስነ ስረአቱ ላይ በስፋት ይለበሳል። ቁሳቁስበፈለገ ብርሃን ወረዳ የሰርግ ስነስርዓት ውስጥ አንዲት ሴት ሞሰብ ወርቅ መያዟ ብቻ ለሰርጉ መዘጋጀቷንን እና ሙያዋን ይጠቁማሉ ። ግብአተ ድምፅ ፣ የተለያዩ ባህላዊ መሳሪያዎች በመጠቀም የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነስረዓትን ያደምቃሉ ። የሚና ክፍፍል የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነስረዓት ላይ ሙሽሮች ፣ ቤተሰቦች ፣ ሽማግሌዎች ሰፊ ሚና ይወስዳሉ ።

በአጠቃላይ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአማራ ክልል፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን፣ በፈለገ ብርሃን ወረዳ ውስጥ በሚከወነው የሰርግ ስነስርአት ላይ በትውፊታዊ ተውኔት ውስጥ ያሉትን አላባውያን በጥናቱ ውስጥ ተንትኗል ።

## 4.2 የመፍትሔ ሀሳቦች

ይህ ፈለገ ብርሃን የሰርግ ስነ ስረአት አሁን ላይ ማሕበረሰቡ ትኩረት እየሰጠው እንዳልሆነ አጥኚው በጥናቱ ተረድቷል።የወረዳው የሚመለከተው አካልም ይህን ባህል ትኩረት ሲሰጠው አልታየም።በመሆኑም የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ባህሉን በመመዝገብ እና በተለያዩ መንገዶች ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ እንዳለበት አጥኚው ተረድቷል።ለምሳሌ፦ ስረአቱን በቴአትር መልኩ በማዘጋጀት ለአከባቢው አልፎም ለሀገሪቱ ማሕበረሰብ የሚያስተዋውቅበት መንገድ ቢመቻች፤እንዲሁም የፈለገ ብርሃን የሰርግ ስረአት በሚደገስ ሰርግ ላይ በመገኘት ድርጊቶችን በምስል ቀርፆ በማስቀመጥ ለሌሎች የማሕበረሰብ ክፍል ማሳየት። በተጨማሪም የባህል ዝግጅት በማዘጋጀት እና እንግዶችን በመጋበዝ ባህሉን ማስተዋወቅ ይኖርበታል።ማህበረሰቡም በተለይ ወላጆች ለልጆቻቸው የባህሉን ጠቃሚ ገፅታዎች ማስተማር እና ማሳወቅ አለባቸው።እንዲሁም ደራሲያን ባህሉን በማጥናት በመፀሀፍ መልኩ ለትውልዱ ቢያሳውቁ ስረአቱ እንዳይጠፋ ይረዳል ። በማለት አጥኚው የመፍትሔ ሀሳቡን ያስቀምጣል።

## ዋቢ መፃህፍት

መቅደስ ሞገስ፡፡(2011)፡፡ወልቂጤ ዩንቨርሲቲ ቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናታዊ ጹሁፍ፡፡የፊጫሳ አምልኮ ስነ ስረዓት ከትዉፊታዊ ተዉኔት አላባዊያን አንጻር፡፡ (ያልታተመ)

ምድራዊት እንዳለ ፡፡(2013)፡፡ወልቂጤ ዩንቨርሲቲ ቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናታዊ ጹሁፍ፡፡የሀሩ የቡሄ በዓል አከባበር ከትዉፊታዊ ተዉኔት አላባዊያን አንጻር፡፡ (ያልታተመ)

ሰዋየዉ ለገሰ፡፡(2010)፡፡ወልቂጤ ዩንቨርሲቲ ቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናታዊ ጹሁፍ፡፡ የኦሮሞ ጎጂ የጋብቻ ስነ ስረዓት ከቃለ ተዉኔትና ከመቸት አንጻር፡፡ (ያልታተመ)

ፋንታሁንእንግዳ ፡፡ (1993)፡፡ተውኔታዊ መዝገበ ቃላትና ብያኔዎቻቸው ከ ሀ እስከ ፐ፡፡አዲስ አበባ ፡፡ ብረሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ፡፡

........................፡፡(2005)፡፡የተዉኔት አጻጻፍ ዘዴ፡፡አዲስ አበባ ፡፡ ብረሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ፡፡

አለም እሸቱ ። (1994)።መሰረታዊ የምርምር እና የዘገባ አፃፃፍ ዘዴ።አዲስ አበባ። ቅድስት ማርያም ኮሌጅ የልብራል አርትስ ፋካልቲ ህትመት ።

ያለውእንዳወቀ ። (2009) ። የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር።አዲስ አበባ ። ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት ።

ዘሪሁን አስፋው ። (2005) ። የስነፅሁፍ መሰረታዊያን ። አዲስ አበባ ።ንግድ ማተሚያ ድርጅት ።

አዲስአለም አስቻለው ። (2010) ።ንግስት ዘውዲቱ ታሪካዊ ተውኔት ። አዲስ አበባ ። ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት ።

ሳሙኤል ተስፋዬ ። (2012) ። የመድረክ ጆርባ ጥበባት ። አዲስ አበባ ።ማይቢቲ ማተሚያ ቤት ።

ደበበ ሠይፉ ። (1973) ።የቲያትር ጥበብ ከጸሓፊ ተዉኔት አንጻር።አዲስ አበባ። ንግድ ማተሚያ ቤት።